# ምዕራፍ ፮

# የሐዋርያዊው ሩጫ ማጠቃለያ
# ፲፱፻፹፮ -፲፱፻፺፰



## ስቀለው! ስቀለው!

የተሳሳተ አቀራረብ ይዞ በወጣው መጽሐፍ ውስጥ የነበሩትን ሕጸጾች በተመለከተ፤ ቢቻል የመጽሐፍ ቅርጽ ከመያዙ በፊት፤ ባይቻል ደግሞ ከታተመም፥ ከተሰራጨም በኋላ ቢሆን ማየትና ማረም ይቻል ነበረ፡፡ ይህንን ለማድረግ ቢያንስባቸው እንጂ የማይበዛባቸው ብዙ ዓይናሞች ሊቃውንት ባሉበት አገር፤ ዓይነ ስዉሩ የእኔ አባት ቀድሞ ማየቱ የሃይማኖት ጉዳይ ምን ዓይነት ጥልቅና ረቂቅ መሆኑን ከመግለጡም በላይ ወደ ውጪ የፈጠጡ ሥጋዊ ዓይኖች ሳይሆኑ ስዉራን መንፈሳዊ ዓይኖች የሚመረምሩት መሆኑን የሚያስገነዝብ ይመስለኛል፡፡ በሌላም በኩል ደግሞ ነገረ ሃይማኖትን በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ለመረዳትና ለማስረዳት ጥልቅና ረቂቅ በሆኑት የአብነት ትምህርት ቤቶች ማለፍ ግድ መሆኑን ያጠይቃል፡፡

በተጨማሪም መንፈሳዊ ጸጋን ለመጐናጸፍ መሠረቱ ዓለማዊ ልዕልና ሳይሆን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይሄንን የምለው በአባቴና በሌሎች መካከል የማውቀው ልዩነት ይህ በመሆኑ ነው፡፡ ሁለት ተጻራሪ ጐራዎች የተሰለፉ ይመስሉ የነበሩት የቤተ ክህነቱ ባለ ሥልጣናትና አባቴ ከሚግባቡት የሚለያዩበት ነገር እየበዛ በመሄዱ ምክንያት ከጥር ወር ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በኋላ አባቴን ከሥራ ገበታው ላይ ለማባረር ቀደም ብሎ የተወሰነው ሐሳብ ገፍቶ መጣ፡፡

የጥቅምቱን ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንዴት እንዳለፉት የሚያውቁት ፓትሪያርኩና ደጋፊዎቻቸው የግንቦት ጉባዔ ከመምጣቱ በፊት ሐሳባቸውን ለማስፈጸም ይረዳቸው ዘንድ ሶስናን ለእደ ረበናት አሳልፎ እንደ ሰጣት ያለ የሐሰት ጉባኤ በማደራጀት በቤተ ክህነቱ መዋቅር ውስጥ የሌለ "የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ" የሚባል ቡድን አቋቋሙ፡፡ በዓለማዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ክፍል የነበሩ ሕጐች የማያውቁት ይህ ኮሚቴ የፓትሪያርክ አባ ጳውሎስንና የአባ ገሪማን መብትና ክብር ብቻ ለማስጠበቅ እንጂ ለሃይማኖት የቆመ በማያስመስል አሠራር ያላስፈውን ውሳኔ ይፋ አደረገ፡፡ በዚህም ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ስለ አገሩ ስለ ኢትዮጵያ ክብር ሲደክም የኖረውን አባቴን

ከሥራና ከክህነት ሥልጣን እንዲባረር የሚጠይቅ የውሳኔ ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ አቀረበ፡፡

በሠላሳ ገጾች የተጠቃለለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.የተጻፈ ሲሆን የአባላቱን ስምና በኮሚቴው ውስጥ የነበራቸውን የሥራ ድርሻ በዝርዝር ያሳያል፡፡ ጉባዔው ዐሥራ ስድስት አባላት የነበሩት ሲሆን ስማቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

፩/ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል
፪/ መልአከ ሰላም ገብረ ሚካኤል በየነ
፫/ ሊቁ ብርሃኑ መኰንን
፬/ መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ
፭/ ሊቀ ሥልጣናት ገብረ ማርያም አጽብሐ
፮/ ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
፯/ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዩ
፰/ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን
፱/ ዲያቆን ያሬድ ከበደው
፲/ አቶ ፀጋዬ በርሔ
፲፩/ መምሬ ፍስሐ ተበጀ
፲፪/ መልአከ ኃይል ቃለ ጽድቅ እውነቴ
፲፫/ መልአከ ሕይወት ወልደሰንበት አድኃን
፲፬/ መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ
፲፭/ መምህር ሰሎሞን ገብሩ
፲፮/ መጋቢ ሥርዓት ዮሐንስ ናቸው፡

ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል የጉባዔው ሊቀመንበር፣ መልአከ ሰላም ገብረ ሚካኤል በየነ ምክትል ሊቀመንበር እንዲሁም መጋቢ ሥርዓት ዮሐንስ ጸሐፊ ሆነው ሠርተዋል፡፡



የስብሰባው ቃለ ጉባዔ እንደሚያሳየው ጉባዔው "የሕግና የውሳኔ አስፈጻሚ ኮሚቴ" እና "የጥናትና የአስተዳዳር አጥኚ ኮሚቴ" የሚባሉ ሁለት ኮሚቴዎች ነበሩት፡፡ የዕለቱ ስብሰባ ሁለቱ ኮሚቴዎች አጥንተው እንዲያቀረቡ ከዐቢይ ኮሚቴው የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተወጥተው ያቀረቡት ጥናት ካለ አዳምጦና መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት እንደነበር ተመዝግቧል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ የዐቢይ ኮሚቴው ቃለ ጉባዔ እንሚከተሰው አስፍሮታል፡፡

ጉባዔውም በጉዳዩ ላይ ከተወያየ በኋላ በሕግና ውሳኔ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተረበው ጥናት በንባብ እንዲሰማ አድርጎ የቀረበውን ሃያ አንድ ገጽ ጽሑፍ በጥሞና አዳምጧል፡፡ ጉባዔው ጥናቱን በንባብ ካዳመጠ በኋላ ማስተካከያና ማሻሻያ ጨምሮ እንዳለ ያጸደቀው ሲሆን ግልባጩም ለቅዱስ ሲኖዶስ ከዐቢይ ኮሚቴው ቃለ ጉባዔ ጋር እንዲቀርብ ተስማምቷል፡፡

ይኸው ሰነድ እንደሚያሳየው ከሆነ ጉባዔው በጥናቱ ላይ ሰሰተነሡት ዐበይት ነጥቦች በሰፊት ተወያይቷል፡፡ የደረሰበትን ግንዛቤ ሲገልጽም "አለቃ አያሌው ታምሩ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጥቅምት ፲፯ ቀንና ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቧቸው ደብዳቤዎች፣ በግል ጋዜጦችና የኘሬስ ውጤቶች፣በውጭ አገር የሬዲዮ ጣቢያዎች ያቀረቧቸው ቃለ ምልልሶች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕልውና የሚፈታተን እንድነቷን የሚያናጋ ምዕመናንን የሚከፋፍል፤ ለጠላት አሳልፈው ለማጋለጥ ሆን ብለው የፈጸሙት የጀርባ ተልዕኮ ያለበት መልእክት የቤተክርስቲያኒቱን መሪዎችቅዱሳን አባቶችን ንጹሕና ቅዱስ ስም የሚያጉድፍ መሆኑን ተገንዝቦአል፡፡ "የሚል የማጠቃለያ ሐተታ ይገኝበታል፡፡በጉዳዩ ላይ አሳለፍኩ ያለው ውሳኔም፤

"...የተፈጸመውን በደል ከቀኖና ቤተ ክርስቲያንና ከአገሪቱ ሕግ ጋር አገናዝቦ አስፈላጊውን ውሳኔ ማሳለፍ የሚያስፈልግ መሆኑን ተረድቶ በሁለት ክፍል ተከፍሎ ስቀኖና ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሊወሰነው የሚገባውንና በአስተዳደር እና በሕጋዊ ፍትሕ የሚፈጸመውን ለይቶ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፎአል፡፡" ይላል፡፡

የቅሬታ አስወጋጅ ኮሚቴ የተባለው ቡድን ከላይ የተጠቀሰው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ከመድረሱ በፊት ጉዳዩን በዝርዝር አይቻለሁ ለማለት በቃለ ገባዔው ውስጥ ያስፈረው ዝርዝር ሒተታ እንኳን ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከማንም በማይጠበቅ የቋንቋ አጠቃቀም የተጻፈ ነው፡፡ ጠቅላላ አቀራረቡ ከባህል፣ ከህዝባዊና ከሃይማኖታዊ ሕግጋት እንጻር ሲታይ እንደ ቤተ ክህነት ካሰ መንፈሳዊ ተቋም መውጣቱን ለማመን የሚከብድ ሰነድ በመሆኑ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር ሲባል ይፋ ባይወጣ ይሻላል የሚል ሃሳብ አድሮብኝ ነበረ፡፡

ነገርግን ስለ ቤተክርስቲያኒቱ እምነት ዋነኛ ተጠያቂ የነበረው የሊቃውንት ጉባዔ ስለ ፈረሰበት ሁኔታና የሊቃውንቱ ጉባዔ ሰብሳቢ የነበረው አባቴም ከቤተ ክህነት እንዲወጣ ስለተከናወነው የአመጽ አሰራር ህዝበ ክርስቲያን ያውቅ ዘንድ ተገቢ ነው የሚለው እምነቴ አመዘነበኝ፡፡ የዘመኑን ቀያፋና ሃና ለማስደሰት ብቻ ሲባል "ስቀለው፣ ስቀለው"እያሉ ከሎሌ አይሁድ ድምጽ የማይተናነስ የግፍና የሐሰት ጩኸት የያዘው ቃለ ጉባዔምለኢትዮጵያውያንና ለታሪክ ፍርድ ይቀርብ ዘንድ የዚህ መጽሐፍ አባሪ ሰነድ በማድረግ አቅርቤዋለሁ፡፡

እንደ አባቴ ያሉ የክርስቶስ ባሮች የጌታቸውን የአምባላቸውን፣ የመረያቸውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አሠረ መስቀል መከተላቸው ተገቢ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ነገርግን በአባቴ ላይ የተፈጸመው ሁሉ በግለሰባዊ ህይወቱ ላይ ብቻ የተፈጸመ አልነበረም፡፡ የሊቃውንት ጉባዔ ኃላፊነቱን ተከትሎ የነበረበትን ተልዕኮ በመወጣት ላይ እያለ ስለ ቤተ ክርስቲያን ህልውናና ክብር የከፈለው ዋጋ በመሆኑ ይህ ታሪክ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ነው፡፡

የቅሬታ አበወጋጅ ኮሚቴ ውሳኔውን ያስተላለፈው ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ መሠረት ያደረገውና ከሥራ መባረሩን የሚገልጠው በስድብ የተሞላ ሁለት ገጽ ደብዳቤ ደግሞ በማግስቱ ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በአባ ገሪማ ተፈርሞ ደረሰው፡፡ ከሃያ አራት ሰዓታት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ በተከናወነው



የኮሚቴው ውሳኔና በአባ ገሪማ ደብዳቤ መካከል የሲኖዶስ ሰብሰባ ይደረግ አይደረግ የሚያሳይ ምንም ዓይነት መረጃ አላገኘሁም፡፡

አባ ገሪማ በጻፉት ደብዳቤ ላይ እንደ ተገለጠው፣ ኮሚቴው መረመርኩኝካላቸው ነጥቦች ውስጥ አምስቱን ብቻ ነጥለው አውጥተው ኮሚቴው በወሰነው መሠረት "ከሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራና ከደመወዝ የተሰናበቱ መሆኑን እናስታውቃለን፤" በማለት ኮሚቴው እስከ ወሰነበት ቀን ድረስ ሊያገኝ ይገባው የነበረውን የሚያዝያን ወር ደመወዝ እንኳ ሳይቀር በመከልከል በአረጋዊ ጉልበቱ በሕዝብ ትራንስፖርት እየተጋፋ ከተከለ ሃይማኖት እስከ ቅድስት ማርያም ድረስ በመመላለስ የሠራበትን የድካሙን ዋጋ ቀምተውታል፡፡ አባቴ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሆኖ ሲቀጠር ለመጀመሪያ ጊዜ የተቆረጠለት ደመወዝ ሃምሣ ብር ነበረ፡፡ ከሥራ በታገደበት ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ይከፈለው የነበረው የወር ደመወዙ ሰምንት መቶ ብር የነበረ ሲሆን አንድ መቶ አርባ አምስት ብር የመንግሥት አበልነበረው፡፡

የእገዳው ደብዳቤ ከደረሰው በኋላ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ለቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና ለአባ ገሪማ ሁለት ደብዳቤዎች ጽፏል፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና መጣስቀደም ብሎ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ለቅዱስ ሲኖዶስ የጻፈውን አቤቱታ በድጋሚ በማስታወስ የተወሰደበትን እርምጃ ተቃወመ፡፡

ለዓመታት የተቀነባበረው ሴራ ግቡን በመምታቱ"አመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥንተ አብሶ አለባት" ብለው የጻፉ፤ "ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኩሉ ጉባዔ በሐዋርያት፣ ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡"እየተባለ ለዘመናት የተሰበከባትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ረግጠው የኢኩሚኒዝምን እምነት የሰበኩና ይህንኑ ትምህርት በመጽሐፍ አሳትመው ያወጡ ሰዎች በየደረጃቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክና የሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ ሆነው በተቀመጡበት አገር፤ ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ አባቴ አለቃ አያሌው ታምሩ ግን እናት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉ

ካስቀመጠችበት የኃላፊነት ወንበር ላይ ተገፍቶ ወጣ፡፡ አባቴ ከሥራ መታገዱን በተመለከተ ከአባ ገሪማ የተጻፈለትን ደብዳቤ አስመልክቶ ሲኖዶስም ለአባ ገሪማም የጻፋቸው አቤቱታዎች ምንም መልስ ሳያገኙ ቀሩ፡፡ አባቴም ከዚያ ቀን በኋላ በመኖሪያ ቤቱ ተወስኖ ለመኖር ተገደደ፡፡



## አሁን ተመቸኝ

**አባቴ ከነበረበት ክርስቲያናዊ ግዴታና በሕግ በተሰጠው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት የቤተ ክርስቲያኒቱን ቀኖናና ሥርዓት ለማስከበር ባደረገው ጥረት ምክንያት እንደ አጥፊ ተቆጥሮ ከቤተ ክህነት መገለሉና ከጡረታ መብት መታገዱ የብዙ ሕዝብንና የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት የሳበ ነበረ፡፡ በመሆኑም በጊዜው ይጻፉና ይታተሙ ከነበሩ ጋዜጦች አንዱ የሆነው "ሞገር" ጋዜጣ በአባቴ ላይ የተፈጸመውን ድርጊት አስመልክቶ አስተያየት ሰጥቶ ነበር፡፡**

"የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አመራር ከጅምሩ ብዙ መሰናክል የገጠመው ከመንግሥት ጋር ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ያላሰለሱ የቤተ ክርስቲያኒቷ ወገኖች ለስደት በቅተዋል፡፡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ከሥራቸው ተባረዋል፡፡ ለአብነት ያህል በኀምሳ ዓመት የሥራ ዘመን ውስጥ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓይን ሆነው ያገለገሉት አለቃ አያሌው ታምሩን ማንሣት ይቻላል፡፡ እጅግ በርካታ የሃይማኖት ተከታዮች ያውቋቸዋል፡፡ እኚህ ሊቅ ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሚለዩበት ጉዳይ ቢኖር በየዘመኑ የተነሡትን ስሕተቶች በዐደባባይ በመተቸታቸው ብሎም በማስተማራቸው ነው፡፡ ይሁንና የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴውፍሎስ አስተዳደር ግን ይህን ሁኔታ በዝምታ ሊመለከት ወይም የቀረበለትን ትችት ለማረም ባለመቻሉ የሊቃውንት ጉባኤ ፈርሶ አለቃ አያሌውን ከሥራቸው እንዲባረሩ አድርጓል፡፡" በማለት ሁኔታውን ገልጾታል፡፡

አባቴ ከሥራ ገበታው ቀርቶ በቤት ውስጥ ብቻ ለመዋል በተገደደባቸው ዐሥራ አንድ ዓመታት ከቤተ ክህነት ተባረርኩኝ፣ ደመወዝ ወይም ጡረታ የለኝም ብሎ ሐዋርያዊ ተልእኮውን አላቋረጠም፡፡ በተለይም መጻሕፍትን በመድረስ ረገድ አባቴ ረጅም ዓመታትን ካሳለፈበት ከቤተ ክህነቱ የሥራ ዘመን በተሻለ ሁኔታ ብዙ መጻሕፍትን ለማዘጋጀትና ለማሳተም ዕድል አግኝቷል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው አቶ ሙሉጌታ ገብረ ወልድና ባለቤታቸው ወ/ሮ ሙሉ እመቤት ተሾመ ባደረጉለት ከፍተኛ እርዳታ ነው፡፡ በሥጋ የተወለድን ልጆቹ ደግሞ በቃሉ

የሚነግረንን ወደ ጽሑፍ በመቀየር ረገድ ከእኛ የሚፈልገውን ድጋፍ ለመስጠት ሞክረናል፡፡

አባቴ በዚህ መልክ የሚያዘጋጃቸው መጻሕፍት በበጐ አድራጊ ምእመናን ድጋፍ ከታተሙ በኋላ ወደ ሕዝብ ለማሰራጨት የገጠመው መሰናክል ነበረ፡፡ ይኸውም በአብያተ ክርስቲያናት ቅጽረ ግቢ ውስጥ እንዳይሸጡ መከልከሉ ነው፡፡ መጻሕፍቱን ለመሸጥ የሚወስዱ የመጻሕፍት ነጋዴዎች በአብያተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢና አካባቢ እንዳይሸጡ ይባረሩ ስለበረ መጻሕፍቱን የሚሸጧቸው ከቤተ ክርስቲያን ራቅ ባሉ መሸጫ ስፍራዎች ብቻ ነበረ፡፡

በዐሥራ አንዱ ዓመታት ውስጥ ጽፎ ያሳተማቸው መጻሕፍት ፩ኛ/ የጽድቅ በር፣ ፪ኛ/ ምልጃ ዕርቅና ሰላም፣ ፫ኛ/ መልእክተ መንፈስ ቅዱስ፣ ፬ኛ/ተአምርና መጽሐፍ ቅዱስ፣ ፭ኛ/ መላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ፣ ፮ኛ/ ዜና ሕይወት ዘቅድስተ ቅዱሳን እመ አምላክ፣ ፯ኛ/ ሃይማኖትና መጻሕፍት የተሰኙ ሲሆኑ ከተራ ቁጥር ፯ በስተቀረ ሁሉም ታትመው ለምእመናን እንዲዳረሱ ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከብዙዎች የሃይማኖት መምህራን በተለየ ሁኔታ ከጋዜጦች የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች አብራርቶና አፍታቶ መልስ በመስጠት ረገድ አባቴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ጋዜጠኞች ለሚያነሡአቸው ጥያቄዎች መልስ በመስጠት በእነሱ አማካይነት ብዙ ትምህርት ለማስተላለፍ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህ ረገድ ከ አንድ መቶ ሃምሳ ያላነሱ ቃለ መጠይቆችን ከተለያዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ጋር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ዘወትር ቅዳሜና ነሙስ ዕለት በመደበኛነት የሚያስተምራቸው ተማሪዎች ነበሩት፡፡ እነዚህን ተማሪዎች በሚያስተምርበት ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስን ቅደም ተከተል መሠረት ያደረጉት ትምህርቶቹ በመቅረጸ ድምፅ ተቀርጸው እንዲቀመጡ አድርጓል፡፡ በዚህ መልክ የተቀረጹት የድምፅ መዛግብት ከአምስት መቶ ያላነሱ ናቸው፡፡



በየዕለቱ በሚነግ እስጥ አገባ ምክንያት ከቤተ ክህነት ሰዎች ከሚደርስበት ጫና ነጻ ሆኖ ለመሥራት በመቻሉ አባቴ ብዙ መጻሕፍትን ለመድረስ ችሏል፡፡ የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም ምእመናንን በማስተማር፣ በመምከርና፣ በመገሠጽ ያስተላለፋቸው ትምህርቶችም ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህን ሥራዎች ለመሥራት ስለ አገኘው ነጻ ጊዜ ሲናገር"ውሻ እየሰረቀች አስቸገረችን ብለው ሰዎች ጆሮዋን ቢቆርጧት፤ እሰይ! ክቦሀቃ[59] ለመግባትማ አሁን ተመቸኝ አለች ይባላል፡፡ ሰዎች አልተመቸኸንም ብለው ከሥራ ገበታ ቢያባርሩኝ ለእኔ ከቀድሞ ይልቅ ዛሬ ለሥራ ተመችቶኛል፡፡ በስንፍና የማሳልፈው ጊዜ የለም፡፡

በይሉኝታ የማላልፈው ሰዓትም የለም፡፡ በሥራ ገበታዬ በነበርኩ ጊዜ የጽሕፈት መሣሪያ ስጠይቅ የዕቃ ግምጃ ቤቱ እርሱ ምን ያደርገዋል? እያለ እስክሪብቶ፣ እርሳስና ወረቀት እንኳ ሲከለክለኝ ለበላይ አመልክቼ መልስ ያጣሁበትን ጊዜ ሳስታውሰው ከዛሬው ጋር ሳነጻጽረው ይገርመኛል፡፡"በማለት በጊዜው የተሰማውን ስሜት " ምልጃ ዕርቅና ሰላም" በተሰኘ መጽሐፉ ገጽ ፱ ላይ ገል ጾታል፡፡

[59] ቦሀቃ ፕለእንጀራ የሚሆን ሊጥ የሚቦካበት ዕቃ "ቦሀቃ " ወይም "ቦሀዕቃ" ይባላል። ምናልባት "የቡኮ ዕቃ" ከሚለው የወጣ ይሆናል።

# ብሔራዊ መብትን ፍለጋ

አባቴ ከሥራ ገበታው ላይ መነሣቱን የሚገልጥ ደብዳቤ በደረሰው በሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ማግሥት ለአባ ገሪማና ለቅዱስ ሲኖዶስ የጻፏቸውን አቤቱታዎች ምላሽ ለማግኘት ጠብቋል፡፡ ለአስቸኳይ ስብሰባ ትፈለጋላችሁ ተብለው ከየአገረ ስብከታቸው የተጠሩት ሊቃነ ጳጳሳት በአባቴ ጉዳይ ላይ አንዳች ነገር እንደሚሉ እየተጠበቀ ነበር፡፡ ነገርግን ከሚያዝያ ፳፱ ቀን እስከ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ድረስ በልዩ ልዩ ምክንያት ሲጉላሉ ከቆዩ በኋላ ስብሰባው አልቋል ተባለ፡፡ ምን ሠርቶ ምን ወስኖ እንደተበተኑ ከቤተ ክርስቲያን ወገን አንዳች ነገር ሳይሰማ መንግሥታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.ባወጣው ዕትሙ ላይ"ወጣቱ ትውልድ ለአገሩ ታማኝ፣በሥነ ምግባር የታነጸ ሆኖ ለልማት እንዲዘጋጅ ሲኖዶሱ ወሰነ" የሚል መግለጫ ይዞ ከተፍ አለ፡፡

አባቴ ይህንን ድርጊት አስመልክቶ "መብሩክ" ለተባለ ጋዜጣ በሰጠው ሐሳብ፤

"...የሃይማኖት ውዝግብ እያለ፣ ፓትሪያርኩ ገደብ አልፈዋል፣ ሙግዚት ጥሰዋል፣ እየተባለ፤ አቤቱታ ቀርቦ እየተሰተጋባ፣ የኑፋቄ መጽሐፍ መበተኑ ምእመናንን አሳዝኗቸው አቤት! አቤት! በማለት ላይ እያሉ፣ በሰላማዊ ሠልፍና በሕዝባዊ ስብሰባ ላይ እየጠየቁ ፣ ይህ እረም ተጭኖበት የሲኖዶሱ ውሳኔ ግን ወጣቶችን ለልማት የሚያዘጋጅ ነው የሚል መልስ መስማት የሃይማኖታዊው ጥያቄ ፖለቲካዊ መልስ ማግኘቱ ፣ በፖለቲካው መልስ መወሰኑና መደምደሙ እኔን ብቻ ሳይሆን የመላው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ምዕመናን በጥልቅ ኀዘን የወጋ ነው፡፡ በጥልቅ ኀዘን የነደፈ ነው፡፡ " በማለት ሀዘኑን ገልጧል፡፡

ለመሆኑ የትኛዋ ቤተ ክርስቲያን ናት ልማትን እንድትሰብክ የታዘዘችው? ይህስ መልእክት ያለው በየትኛው ወንጌል ነው?" በማለትም ጥያቄ ሰንዝሯል፡፡በተጨማሪም በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ



፳፱ በቁጥር ፬ እና ፭ የተጻፈውን የሙርጉን ባለቤት ጥሬና ለሙርጉ የተጠሩ ታዳሚዎችን ሁኔታ በማስታወስ፤"ወደ እርሻ፣ ወደ ንግድ፣ ወደ ወትድርና የተሰማራ የወንጌል ሰባኪ ማን ነው? እርሻ እንዲያርሱ ንግድ እንዲያስነግድ የተላከ የወንጌል ሰባኪ ማን ነው? የትኛው ሐዋርያ ነው? በማለት ሁለተኛ ጥያቄ ሰንዝሯል፡፡ ከዚህ በማስከተልም "አንድ የቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በሃይማኖት ጉዳይ ላይ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ላይ ሊወያይ በአስቸኳይ ተጠርቶ ከመጣ በኋላ ወጣቱ ለአገሩ ታማኝ ሆኖ ለልማት እንዲዘጋጅ ወስኖ ተበተነ ብሎ ማወጅ፤ እንኳን ለሌላ ሰው ጆሮ ለሰይጣን ጆሮም የሚስማማ አይመስለኝም፡፡" እስከማለት ድረስ የተሰማውን ኀዘን ገልጧል፡፡

ስሁለት ወር ከሃያ ስድስት ቀናት ያህል መልስ ከጠበቀ በኋላ ብሔራዊ መብቱን ማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘው እምነቱን በነጻነት የማራመድና፣ ሠርቶ የመኖር መብቱን በጠራራ ፀሓይ የገፈፉትን የቤተ ክህነት ባለ ሥልጣናት ወደ ሕግ ዐደባባይ ይዞ በመቅረብ ለመፋረድ ወሰነ፡፡ ይህን ሲያደርግ ሲወስን ዋነኛ የእምነቱ መሠረት ያደረገው ያኔ ገና በወጣትነቱ የጭቃ ሹምነት ተራውን እንዲያስከብር፣ የዓይነ ሥውርነት መብቱን እንዲጠይቅ ይገፋፋው የነበረውን የባለአገርነት መብቱን የመፈተን እምነት እንጂ ሰማቀርበው ክስ ፍትሕ አገኛለሁ አላገኝም በሚል እሱተሳሰብ አልነበረም፡፡

በዚህ ውሳኔው መሠረት ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ክስ አቀረበ፡፡ በክሱ ላይ እንደ ተመለከተው አባቴ ለ፶ ዓመታት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጠቱ የተጠቀሰ ሲሆን ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይኖርበትና ማስጠንቀቂያም ሳይሰጠው ከሥራና አገልግሎቱ ማግኘት ከሚገባው ደመወዝና ማንኛውም ጥቅም ሚያዝያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በተጻፈ የሥራ ስንብት ደብዳቤ እንዲገለል መደረጉ አግባብነት የሌለው መሆኑን ገልጿል፡፡

በክሱ ሂደት የመጨረሻ ለነበረው ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው የይግባኝ መልስ ላይ እንደመግቢያ ባቀረበው ጽሑፍ፣ ከልጅነት እስከ እውቀት

ለአገር፣ ለወገንና ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተውን አስተዋጽኦ በማጠቃለል አስፍሯል፡፡ ወደ ፍርድ ቤት የሄደውም ከብሔራዊ መብቱ የሚመነጨውን እምነቱንና የሥራ ኃላፊነቱን በነጻነት ለመወጣት እየሠራ ሳለ ቤተ ክህነቱ ከሥራው፣ ከደመወዝና አልፎ ተርፎም ከጡረታ መብቱ ስላገደው መሆኑን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም እሱን ከሥራ ለማሰናበት በተጻፈው ደብዳቤ ላይ እንደ ተገለጠው ሳይሆን በቤተ ክህነት ባሳለፋቸው አገልግሎት ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ለምትመራበት ቀኖና ለእውነተኛው እርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ባለው ትምህርትና ችሎታ መሠረት በቅንነት ማገልገሉንና የቤተ ክርስቲያንን ሕጋን ሥርዓቷን አስከብሮ ንጹሕ የወንጌል ትምህርትን ከክሕደትና ከኑፋቄ ከፖለቲካም ለይቶ በማስተማሩ አንድም ቀን የቃልም ሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ደርሶት እንደማያውቅ በመግለጥ ወደ ሥራው የመመለስ መብቱ እንዲከበርለት ማመልከቱን አብራርቷል፡፡

ወደ ለበር ሰሚ ችሎት የቀረበበትን ጉዳይ አስመልክቶ በሰጠው መልስ ደግሞ ቤተ ክህነቱንም ሆነ ማንንም የሚጐዳ ሥራ አስመፈጸሙና ሥራውንም በአግባቡ ይሠራ እንደነበረና በተለያየ ደረጃ ጉዳዩን ባዩ ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ የመጨረሻው ፍርድ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ የነበረ ደመወዙ እንደከፈለው እወሰኑንም ገልጧል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ ሳለ ወደ ሥራ መመለሱ "የኢንዱስትሪ ሰላምን የሚያደፈርስ በመሆኑ" ሊመለስ አይገባም በሚል ቤተ ክህነቱ ያቀረበው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተቀባይነት ማግኘቱም ህገየሥር ፍርድ ቤቶች የፈረዱለት ደመወዙ እንዲታገድ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለጥ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሐሳቦች ላይ ተመርኩዞ መልስ ሰጥቷል፡፡

- ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የቤተ ክህነት ተቀጣሪዎች ሆነው የሚያገለግሉባት መንፈሳዊ ተቋም መሆኗንና አሲቀና ምንዝር፣ ባለቤትና አሽከር አለመሆናቸውን፤

- በነበረው የሥራ ክፍፍል አባቴን ከሥራ ያገዱት የአስተዳደሩን ክፍል ሲሠሩ እሱ ግን በሊቃውንት ጉባዔ ኃላፊነቱ ሥር የነበረውን የትምህርተ ሃይማኖቱን፣ የመጻሕፍቱን፣ የሕግና የሥርዓት ተጠያቂነቱን ይዞ ሲሠራ መኖሩን፤

- ማንም የቤተ ክርስቲያን አባል ትምህርተ ሃይማኖትን አፋልሶ ከቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት፣ ትምህርትና ሥርዓት ውጪ ተናግሮ፣ ጽፎና ሠርቶ ከተገኘ የሊቃውንት ጉባዔው በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት እርምጃ የመውሰድ መብት እንዳለው፤
- እሱም በዚሁ መሠረት አባ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት በመድፈራቸው አስፈላጊ ጥያቄዎችን ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ላለው ለቅዱስ ሲኖዶስ ማቅረቡን፣ የቀረበውን ጥያቄ አባ ጳውሎስ በሥልጣናቸው ማፈናቸውን፤

- በዚህ ሳይወሰኑ የኑፋቄ መጽሐፍ ማውጣታቸውን፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት ውጪ በባዕድ የሃይማኖት ተቋም ባሕልና ሥርዓት ሚመተ ጳጳሳት መፈጸማቸውን፣ በተመለከተ ስለጉዳዩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ማወቅ ስለነረባቸው ማሳወቁን፤

- ጋዜጠኞች በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ላቀረቡለት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶችን መስጠቱንና ይህም ክርስቲያናዊ ግዴታውና ብሔራዊ መብቱ መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት የተላለፈው ምንም ዓይነት ሕግ አለመኖሩን፣ በየወቅቱ ለሰጣቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎችም ሆነ ጥያቄና መልሶችም ማስተባበያ አቅርበው እንደማያውቁ፤

- የእሱ የሥራ ሹመት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ የተሰጠ ሐዋርያዊና ክህነታዊ ሹመት በመሆኑ የሕይወት ፍጻሜ ከሚገታው በስተቀር የሚወስነው እንደሌለ፣ ወደ ሥራ ሲገባም በጊዜው በነበሩ የአገሪቱ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ዕውቅና ተሰጥቶት መግባቱን፤

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባዔ ሆኖ ሳለ ሕገ ቤተ ክርስቲያንም ሕገ መንግሥትም የማያውቀው ኮሚቴ በሰጠው ፍርድ መሠረት ከሥራው እንዲታገድ መደረጉን፡

- ምንም እንኳ ከቢሮ ቢታገድም ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለምእመናን ባለው ሐዋርያዊ ተልዕኮ ምክንያት ሥራውን ሳያስተጓጉል በቤት ውስጥ ሆኖ እየሠራ መሆኑንና ለምእመናን አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍትን ማሳተሙን፡

- እሱን ለመከራከር የተቀጠረው ጠበቃ "አለቆቹ" /"አለቆቹ" እያለ ለፍርድ ቤት በሰጣቸው መልሶች ላይ እየደጋገመ መጥቀሱም አግባብ አለመሆኑንና በቤተ ክርስቲያን አለቃና ምንዝር ፡ ጌታና ሎሌ አለመኖሩን፤ ይልቁንም እንደ የወንጌል ቃል የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ግንኙነት "እናንተ ሁላችሁ ወንድማማቾች ናችሁ" በሚለው አምላካዊ መመሪያ ላይ የተመሠረተ መሆኑን፡

- በሥጋዊ አስተዳደሩም ቢሆን አንዱ አንዱን በሥልጣን ሊጨቁነውና መብቱን ሊገፈው፣ እሱ እየበላ ሊያስርበውና ሊያጉላላው የማይገባ መሆኑን፡

- የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት በሰውም በቤተ ክርስቲያንም በአገርም በእግዚአብሔርም ላይ የሚፈጽሙት መራራ ግፍና አመጻ ከባድ መሆኑን፡ሰበር ሰሚው ችሎት ተገንዝቦ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተፈረደለት በኋላ በአፈጻጸም የታገደበት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ፍርድ ጠይቋል፡፡

ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. የተመሠረተው ክስ ከብዙ ክርክርና ውጣ ውረድ በኋላ እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የቀረበ ሲሆን በሁሉም ደረጃ ጉዳዩን ያዩት ዳኞች አባቱ ከቤተ ክህነት እንዲባረር የሚያደርስ



ምክንያት ባለ ማግኘታቸው ከሥራ መባረሩ አግባብ እንዳልሆነ ገልጸው ከሥራ ከተባረረበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻ ፍርድ እስከ ተሰጠበት ጊዜ ለነበሩት ዓመታት የተከማቸ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈለው ወስነዋል፡፡ ወደ ሥራው ስለ መመለስ ለተነሣው ጥያቄ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ወስነዋል፡፡ ሆኖም ግን ቤተ ክህነቱ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ሄዶ ለአባቱ የተፈረደለት ውዝፍ ደመወዝ እንዳይሰጠው አሳገደ፡፡ በአንጻሩ አባቱ ደግሞቤተ ክርስቲያን ኢንዱስትሪ ስላልሆነች ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ 'ሕጉ ስህተት አለው እኔንም አይመለከተኝምና ወደ ሥራ ልመለስ ይገባኛል' ብሎ በመጠየቅ ቀደም ብዬ የዘረዘርኳቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች አቀረበ፡፡ ሆኖም ግን ሰበር ችሎቱ የሕግ ስህተት አለ የተባለውን ባለመቀበል የአባቱን ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄ ውድቅ አደረገው፡፡

በቤተ ክህነት ላይ የቀረበው ክስ ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ ከአባቱ ጐን ሳይለዩ፣ አስፈላጊውን ሙያዊ አገልግሎት በነጻ የሰጡት ጠበቃው አቶ ማረን ወንዴ ሲሆኑ በሙያቸው ብቻ ሳይሆን በያንዳንዱ የፍርድ ቤት ቀጠሮ በራሳቸው መኪና የትራንፖርት አገልግሎት ጭምር እየሰጡ ከፍተኛ ድጋፍ አድርገውለታል፡፡

# የእግዚአብሔር ሥርዓት ከሚዛባ የሰው ፈቃድ መለወጥ አለበት

አባቴ ከቤተ ክህነት ሥራው ከታገዱ በኋላ በየሳምንቱ ሐሙስ ከሚሄድበት የማኅበረ በኲር ተማሪዎች ስብሰባ ውጪ እንቅስቃሴው በቤት ውስጥ ብቻ ተወሰነ፡፡ ከኢየንጳንዱ ዕለት ግማሽ ያህሉን የሚያሳልፈው እንግዶችን በማነጋገር ሲሆን ቀድሞ ቀጠሮ የያዘንም ሆነ ያልያዘን ሰው ለማነጋገር ምንጊዜም ዝግጁ ነበረ፡፡ ብዙዎቹ እንግዶቹ ስለሃይማኖት ለመማር የሚመጡ ነበሩ፡፡

ከመደበኛ የጸሎት ሰዓቶቹና እንግዶችንና ተማሪዎችን ከማነጋገር ውጪ የሚተርፈውን ጊዜውን የሚያውለው መጻሕፍትንና ሌሎች ጽሑፎችን በማስነበብና በማጻፍ ነበር፡፡ ከአገር ውስጥና ከውጪ አገር የሬዲዮ ጣቢያዎች የሚተላለፉ ወቅታዊ ጉዳዮችን በመከታተል፣ ከነዚህ ጉዳዮች የሚተርፍ ማንኛውንም ሰዓት ደግሞ የጸሎት ስንቱ ላይ በመጨመር ያሳልፍ ነበረ፡፡

ከቤተ ክህነት ኃላፊነቱ የተነሣ ስሞን ጉዳዩ በብዙዎች ዘንድ መወያያ መሆኑ አልቀረም፡፡ ምእመናን ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች በወቅቱ ይታተሙ በነበሩ ጋዜጦች ደጋግመው መውጣት ጀመሩ፡፡

ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. የወጣው "ጦማር" ጋዜጣ "የእግዚአብሔር ሥርዓት ከሚዛባ የሰው ፈቃድ መለወጥ አለበት" በሚል ርዕስ ባወጣው ዘገባና ቃለ መጠይቅ እንደቀረበው በኢትዮጵያ የታሪክና የሥልጣኔ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጣዊና ውጪያዊ የመሰነጣጠቅ ችግር እየተፈጠረባት መሆኑንና ችግሩም ከውጪ የመጣ ሳይሆን በአመዛኙ ከራሷ የፈለቀ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ሲል በቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳደር ችግር ላይ ቅሬታ ሲያሰሙ የነበሩ ወገኖች የእምነት ችግርን እስመልክቶ



አቡነቴታ አያሰሙ መሆኑ በጋዜጣው ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይኸው ጋዜጣ የፓትሪያርክ አባ ጳውሎስ አመራር ገና ከጅምሩ ብዙ መሰናከል የበዛበት እንደነበረ ገልጦ ችግሩ እንዲቀረፍ ያሳሰቡ የቤተ ክርስቲያኗ ወገኖች ለስደት መብቃታቸውንና ሲቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ከሥራቸው መባረራቸውን በመጠቆም በ፵ ዓመታት የሥራ ዘመን ውስጥ "ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዓይን ሆነው ያገለገሉት አለቃ አያሌው ታምሩን ማንሳት ይቻላል" ብሎ የአባቴን ከኃላፊነት መነሣት እንደ ምሳሌ አሳይቷል፡፡ ጋዜጣው ከዘገባው በተጨማሪ ለአባቴ ያቀረባቸውን ጥያቄዎችና ያገኛቸውን መልሶችም አስፍሮ ነበረ፡፡ ከጥያቄዎቹ አንዱ፤

"እንደሚታወቀው የርስዎ ተቃውሞ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ቀደም ባሉት ጊዜያት እንደነበረም ይታወሳል፡፡ ስለፖትሪያርኮች ሹመት፣ ስለቤተ ክርስቲያኒቷ ሥርዓትና አስተዳደር በተለያዩ ጊዜያት ተቃውሞዎን አሰምተዋል፡፡ የርስዎን ተቃውሞ የሚቃወሙ ሌሎች ወገኖች ደግሞ አለቃ አያሌው እጅግ ድፍረት የሚያበዙና በዕውቀታቸው የታበዩ ሰው ናቸው ይላሉ፡፡ በርግጥ ድፍረት ያበዛሉ? የሚል ነበረ፡፡

ለዚህ ጥያቄ አባቴ የሰጠው መልስ ሰፋ ያለ ሲሆን ለአንባብያን ሊስጥ የሚችለውን ትምህርት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*"እውነታቸውን ነው፡፡ በዕውቀቴ አልታበይም እንጂ ድፍረት አበዛለሁ፡፡ ይህም ወድጄ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው ብያለሁ፡፡ የኔ አይደለም፡፡ እንዴ/ለምሳሌ ጥያቄ ልጠይቃችሁ፡፡ ሰዎች እነሱ የፈሩትን በሌላ ይለካሉ (ይሞክራሉ)፡፡ በሌላ ይመኛሉ፡፡ ሰዎች እሳትን በእጃቸው አይጨብጡትም ግን በመቆንጠጫ ይጠቀማሉ፡፡ እጃቸውን ወደ እሳት አያስገቡም፡፡ነገርግን በማማሲያ ወይም በማንኪያ ይጠቀማሉ፡፡ ታዲያ ያ ማንኪያ ያ ማማሲያ ደፍሮ ነው ያደረገው ማለት ነው እሳት ውስጥ መግባቱን? ወዶ አይደለም ስለተገደደ ነው፡፡ የሰው መሣሪያ ስለሆነ ነው፡፡ ሰዎች ተጠቀሙበት እንጂ ለርሱ ጥቅም አይደለም የተደረገው፡፡ "*

"እኔም መላልሼ እንደምናገረው ራሴ ደካማ ነኝ፡፡ መንገድ እሳዩኝ የምል ሰው ነኝ፡፡ ቀኝም ግራም የማላውቅ ሰው ነኝ፡፡ ሁልጊዜ የሚጐልብኝ ሰው ነኝ፡፡ የጐደለብኝ አንድ አካል ዓይን ነው፡፡ ግን መላውን የሰው አካል ካልተሞላሁ አልንቀሳቀስም፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ ሳለ ግን የእግዚአብሔር መልእክት ሆነና ስለ ቤተ ክርስቲያን በግድ ተናገር ያሰኘኝን እናገራለሁ፡፡ በድፍረት አይደለም የምናገረው፡፡ በእውቀቴ ብዛት አይደለም፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው፡፡ ለምሳሌም በመኃልየ ዘሰሎሞን በመጀመሪያው ምእራፍ ላይ "ደቂቀ እምየ ተበአሱ በእንቲአየ" "የእናቴ ልጆች ስለ እኔ ተጣሉ፡፡ ተከራከሩ፡፡" "እንዘፉኒ ዐቃቢተ አጸደ ወይን፣የወይን ጠባቂ አድርገው ሲሾሙኝ ነበር፣" ግን "አጸደ ወይን ዘዚአየ ኢ ቀብኩ፣የሰጡኝን ወይን አልጠበቅሁትምና በዚህ ምክንያት የእናቴ ልጆች ተጣሉ፡፡[60] የሚል ተጽፏል፡፡ እንግዲህ የቤተክርስቲያን ልጆች ጸብ የሚፈጥሩት፣ ክርክር የሚያደርጉ በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተሾሙ ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስትና ሌሎችም መሪዎች እንዲሁም ደግሞ መምህራን እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ በአስተዳደሩ፣ በትምህርቱ፣ በሥርዓቱ፣ በእምነቱ አንዳንድ ጉድለት ሲያመጡ ሌሎች ደግሞ ይቃወማሉ ይከራከራሉ፡፡ ሕግ ነው ማለት ነው፡፡ "ስለ እኔ ተጣሉ"ይላልና፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በላከው መልእክቱ በምዕራፍ ሁለት ተጠቅሷል፡፡ "ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ በሰዎች ፊት ተቃወምኩት፡፡ ከአይሁድ ከሆኑ ምእመናን ከመምጣታቸው በፊት ከአሕዛብ ጋር በልቶ ነበር፡፡ ከአይሁድ ከሆኑ ምእመናን በመጡ ጊዜ ግን ከነርሱ ስለተለየ ወቀስኩት፡፡" ነው የሚለው፡፡

"እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱስ ጴጥሮስን በድፍረት ለመውቀስ ፈልጐ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት ከሚዛባ የሰው ፈቃድ መለወጥ አለበት ብሎ ነው፡፡ እኛም የምንለው ይሄንኑ ነው፡፡ እንደገናም ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ጴጥሮስ በአንጾኪያ ሲያስተምሩ በነበረበት ጊዜ በደረቁ ተጭነው አሕዛብ አሰሯቸው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስን ጌታ

[60]መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፣ምዕራፍ ፩፥፮፡፡



አደሷችሁ አሁን ጳውሎስን እልካላችኋለሁ አላቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ወዲያውኑ ደረሰና አገኛቸው፡፡ እዚህና ቆዩ እስቲ እንግዲህ ብሎ ወደ ቤተ መንግሥት ሄደ፡፡ ወደ ቤተ መንግሥት ሲሄድ ግን የአገሩ ካህናት የሚለብሱትን ልብስ ለብሶ ነው የሄደው፡፡ እነሱ ደግሞ የአገራቸው ካህን መስሏቸው ተቀበሉት፡፡ እሱም እዚህ አገር የገቡ የክርስቶስ ተማሪዎች አሉ እንዴ ነገሩ ምንድን ነው? አላቸው፡፡ አረ አባታችን እንተም ሳትነግረን ደብድበን ወዲያ ጥለናቸዋል አሉት፡፡ እስቲ አሳዩኝ አላቸውና ሄደው አሳዩት፡፡ ለመሆኑ እናንተ እንደው ይህን ትምህርት ይዛችሁ በየአገሩ ትዞራላችሁ? ምን ኃይል ታደርጋላችሁ?አላቸው፡፡ እነሱም እኛ ሙት እናስነሳለን፡፡ ድውያን እንፈውሳለን፡፡ ልዩ ልዩ ተአምራት እናደርጋለን አሉት፡፡ እሱም ቅዱስ ጴጥሮስን እውነት ሙት ታስነሣላችሁ? አለው፡፡ በዚህን ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱስ ጴጥሮስን ወይድ ቀጣፊ! ብሎ በጥፊ መታው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም "ተመየጥከኑ ጳውሊ ኀበ ዘቀዳሚ ግብርከ፣ጳውሎስ! ወደ ቀደመ ግብርህ ተመለስክ ወይ" እስከ ማለት መድረሱን መንፈሳዊ ታሪክ ይናገራል፡፡"

ሐዋርያት እንኳ እርስ በርሳቸው በምስጢር በቤታቸው በቤተ ክርስቲያናቸው በአደባባይም ቢሆን የወንጌል ሥራ እንዲቃና ብዙ ይጋጫሉ፡፡ ብዙ ይከራከራሉ፡፡ ብዙ ይነጋገራሉ፡፡ ታዲያ እኔ የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ ሆኜ ፴፭ ዓመት የሠራሁ ሰው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ እጅ የተቀባሁ ካህን፣ በቤተ ክርስቲያን ካሉት ሊቃውንት ምንም እንኳ እንደ እነሱ እሆናለሁ ባልልም በመጠኑ ከቁጥር ውስጥ የገባሁ ሰው የቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓትና ትምህርት ሲዛባ ዝም ብሎ መመልከት ይገባኛልን? ጌታዬ ጩህ ፣ ጉሮሮህ እስኪነቃ ጩህ፣ ድምጽህ እስኪጠፋ ጩህ ይለኛል፡፡ የሚቀሰቅሰኝ ይኸው ነው፡፡ እና የተናገርኩት በዚህ ምክንያት ነው እንጂ ከሌላው እበልጣለሁ ብዬ አልተናገርኩም፡፡ አልናገርምም፡፡ የሚበልጠኝ አለ፡፡ የሚያንሰኝም አለ፡፡ ደግሞም ብዙዎቹ አይበልጡኝም፡፡ ሁሉም አያንሱኝም፡፡ አሁን ያሉት መጽሐፉን ያዘጋጁት ግን ከእኔ በታች ናቸው፡፡" በማለት ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡

ስለ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን መልእክት መናገር ግዴታው እንደነበረ አጥብቆ ያምን የነበረው አባቴ በግንቦት ወር ፲፱፻፹፰ ዓም መልእክቱን ለሕዝብ ካስተላለፈባቸው ጋዜጦች ሌላው "መብሩክ" እየተባለ ይጠራ የነበረው ጋዜጣ ነው፡፡ ይኸው ጋዜጣ ግንቦት ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓም "ታላቅ ምስጢር ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ሲገለጥ" በሚል ርእስ ባወጣው ጽሑፍ ከዚህ በታች የሰፈረውን የአባቴን መልእክት አቅርቦ ነበረ፡፡ ይህ መልእክት ከቤተ ክህነት ኃላፊነቱ በታገደ ሰሞን ከህዝብ ለሚጎርፉላቸው ጥያቄዎች መልስ ያፈላልጉ ስለነበረ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥ በተጠየቀው መሠረት የተላለፈ መልእክት ነው፡፡

*"ከሁሉ አስቀድሜ በዚህ ከፍተኛ ጉዳይ ላይ እንድንወያይ የፈቀደልን አምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰው፡፡ ወደዚህ ሩቅና ከፍተኛ መልስ ከመግባቴ አስቀድሞ አንድ አንድ ነገሮችን ባስታውስ ደስ ይለኛል፡፡ አንዳንድ ሰዎች እሱ የአንድ ሰው ያህል እይበቃውም ወይ በቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉዳይ ምን አገባው?ተራ ሰው ነው፡፡ እንደ አንድ ሰው መናገር አይገባውም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች እንደሚያነሱ ዐውቃለሁ፡፡ አንዳንዶችም በመጋፋት ለመታወቅ የማደርገው የሚመስላቸውም አሉ፡፡ እኔ የቤተ ክርስቲያንን ቅድስና፣ በቤተ ክርስቲያንም አማካይነት የሚሰጠውን አያንዳንዱን የክርስቲያን ቅድስና፣ ከዚያም በላይ በሹመት በምርጫ የሚሰጠውን የእበውን፣ እንዲሁም በገድልና በትሩፋት የሚገኘውን የሰማዕታትንና የብፁዓንን ቅድስና እውቃለሁ፡፡ አምናለሁ፡፡ "እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡እሱ የቀደሳቸው ሁሉ ቅዱሳን ናቸው፡፡"ይህ ስለሆነም ማንኛውንም ቢሆን ለመድፈር ለመጋፋትም ፍላጐት የለኝም፡፡ ግን ከሁሉ በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ቅድስና፣ የቤተ ክርስቲያን ቅድስና፣ የሃይማኖት ቅድስና ሲደፈር በጉዳዩ መግባትና የሚፈለገውን ግዳጅ መቀበል ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን ስለማምን ነው፡፡*

*"ጌታ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተገኝቶ በዚያ ሥፍራ ሲሸጡ ሲለውጡ የነበሩትን ሲቃወም ደቀ መዛሙርቱ ያሰቡት "የቤትህ ቅንዓት በላችኝ" ተብሎ ተጽፎ እንደነበረ ነው፡፡ ግን ደግሞ ነቢዩ "አንተን የሚገዳደሩህ ተግዳሮት በላዬ ወደቀ" ይላል፡፡ በዚህ ምክንያት ጌታ ራሱ ለቤተ መቅደሱ በመቅናት ብዙ ጉዳዮች ከፈጸመ በኋላ ደቀ መዛሙርቱንም ምእመናንንም ለእግዚአብሔር ክብር በሚሆነው ሁሉ በአደባባይ በግልጽ እንዲናገሩ እንዲመሰክሩ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡*

*"ከዚህ በቀር በልዩ የሚጠሩ ሰዎች እንዳሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ስፍራ ተጽፏል፡፡ እግዚአብሔር በድምጽ የጠራቸው፣ የላካቸው እንደነሙሴ ያሉ መልእክተኞች ነበሩ፡፡ በራእይ የጠራቸው የላካቸው እንደ ኢሳይያስ እንደ ኤርምያስ እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ ያሉ ነበሩ፡፡ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ የራዕዩን ጥሪ መልስ መላልሶ ይገልጣል፡፡ በግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ በምዕራፍ ፱፥፫ ከተገለጠው ጀምሮ በምዕራፍ ፲፪፥፲፰ እግዚአብሔር በራእይ ጠርቶ ትዕዛዝ እንደሰጠው ይናገራል፡፡ በምዕራፍ ፲፮፥፱ ላይ እንደ መቄዶናዊ መኰንን መስሎ ወደኛ ወደ መቄዶንያ እለፍ እርዳን ብሎ እንደጠራው ይናገራል፡፡ በምዕራፍ ፲፰፥፱—፲፩ እንደተጻፈውም "ጳውሎስ አትፍራ ተናገር፤ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ምንም የሚጎዳህ ነገር የለም።" ብሎ እንዳጸናው ይናገራል፡፡ እንዲሁም ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በሰፊው እንደገለጠው "አንድ ሰው" ይላል "በሥጋው ይሁን በነፍሱ አላውቅም ወደ ሰማይ ተነጥቆ ነበር፡፡ በዚያም ድንቅ ምስጢር አይቷል፡፡ የሰው ልጅ ሊሰማው የማይችለውንም ንግግር ሰምቷል" ይላል፡፡ እግዚአብሔር ነቢያትንም ሐዋርያትንም ከዚያም ወዲህ በጸጋው ብዙዎችን በራዕይም በገሃድም እየጠራ ለመልእክቱ ልኳል፡፡*

*"እኔን አነስተኛ ምስኪኑን በተፈጥሮ ደካማ የሆንኩ በኃጢአትም ከሁሉ የረከስኩትን ደሃውን መላልሶ በራዕይ በመጎብኘት ብዙ ትዕዛዝ ሰጥቶኛል፡፡ አቅሜ የፈቀደውን ያህል ከሥራ ላይ ውለዋል፡፡ ከመጀመሪያው የሃይማኖት ትምህርት ለማስተማር በቂ ነኝ ብዬ አይደለም የጀመርኩት ግን ሕዝቅኤልን፣ ዮሐንስ*

ወንጌላዊን መጽሐፉን አብልቶ ሂዱ አስተምሩ እንዳላቸው፤ እኔንም አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የተጻፈባቸውን መጻሕፍት አብልቶ አስተምር ብሎ ካዘዘኝ ጊዜ ጀምሮ እሱ የሰጠኝን መመሪያ ተቀብዬ በማስተማር ላይ ነኝ፡፡ እስከ አሁንም ድረስ ሌሎች እንደሚሉት ከሰው በኩል ዋጋ አገኝበታለሁ፤ ከሰው በኩል እጠቀምበታለሁ፤ ዛሬ እና እገሌ ይሰሙኛል፤ ዛሬ እና እገሌ ይመለከቱኛል ብዬ በመድረክ ቆሜ አላውቅም፡፡ ምስክሬ እሱ ነው፡፡ በማስተማርም ረገድ አስቀድሞ መጽሐፍን ተመልክቼ ቁጥር ምዕራፍ አገናዝቤ ወጥቼ አላውቅም፡፡ ከመድረክ ላይ ስቆም የገለጸልኝን ብቻ ነው የማስተምረው፡፡ በዚህም እስከ ዛሬ ድረስ የሰው ከንቱ ውዳሴ ቀላቅዬ እንዳላስተማርኩኝ የእሱን መልእክት ለምእመናን እንዳደረስኩኝ እሱ ብቻ ሳይሆን የሚሰሙም የሰሙኝም ሁሉ ይህንን ያውቃሉ፡፡

"መልእክቱ ግዴታዬ እንጂ በፍቃዴ የገባሁበት አይደለም፡፡ መጻሕፍትንም በምጽፈበት ጊዜ የማጽፈውን በቃሌ እየነገርኩ እንደመሆኑ መጠን ሲቸግረኝ ምስጢሩ ሲከብደኝ አቋርጣለሁኝ፡፡ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለክታለሁኝ፡፡ በራዕይ የገለጸልኝን ብቻ ሳልጨምር ሳልቀንስ በጽሑፍ ላይ አሰፍራለሁኝ፡፡ ለምሳሌ ያህል በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. ለዶክተር አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት የሰጠሁትን መልስ "መቼ ተለመደና ከተኩላ ዝምድና" የተባለውን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከሰሙዬው እኒጋገር የተነሣ፤ አንደኛ ሰሙዬው ለአማርኛ ቋንቋ እንግዳ በመሆናቸው፤ ሁለተኛ ከልዩ ልዩ አስተሳሰብ በሚሰጡት የቃላት ክብደት የተነሳ፤ ጥቅሶችን ከቃላቱ ካለመገንዘባቸው የተነሣ፤ በዚያም ብቻ ሳይሆን የተጠቀሱት ቃላት ሁሉ የመጻሕፍት ጥቅሶች ከመሆናቸውም የተነሣ፤በዚያ ምክንያትምበመሀሉ የጸጋን እምነት አቆራኝተው አቅርበው ስለነበረ ይህንን ሁሉ ተንትኖ ለማስረዳት በጀመርኩት ውጥን ከሊቃውንት የምጠቅሰውን ቃሉ የሚያስረዳኝ ቅዱስ ቄርሎስ ነበረ፡፡ ከሐዋርያት የምጠቅሰውን ጥቅስ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ



ያስተምረኝ ነበረ፡፡ከሁለቱ የሰማሁትን ቃል ብቻ ነው በዚህ መጽሐፍ ያሰፈርኩት፡፡ ይህንንም የምገልጥላችሁ ባለፈው የማባረሪያ ደብዳቤ ላይ "በየመድረኩ በየቀመበት ሁሉ ለራሱ ዝና ሲል ፖለቲካውን ከመደቀደቁ በቀር ሌላ ያስተማረው ነገር የለም" ብለው የቤተክህነቱ መሪ ስለጻፉ ነገሩ እውነት አለመሆኑን እንድትረዱት ነው፡፡" በማለት ስለተልእኮው መግለጥ የሚገባውን ለምእመናን አስተላልፏል፡፡

አባቴ በራእይ የተቀበለውን መልእክት ለምእመናን ይፋ ከማውጣቱ በፊት እንደ ቤተክርስቲያን ህግ በለሆሳስና በጥንቃቄ እዚያው በቤተክህነቱ ሰዎች መካከል ለማቅረብ ቢሞክር ሰሚ ማግኘት አልቻለም፡፡ ስለሆነም የጉዳዩ ባለቤት ለሆኑ ምእመናን ይፋ ማውጣትን መረጠ፤ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊ መልእክቶችን በራእይ መቀበል ልክ አዲስ ክስተት እንደሆነ ሁሉ ራሳቸው የቤተ ክህነቱ ሰዎች "...ተኝቶ የቃዠውን ..."ብለው እስከማሾፍና እስከ መዘባበት ደረሱ፡፡ ሆኖም ግን በጉዳዩ ላይ ከቤተክህነቱ ሰዎች የተሻለ ትኩረትና የማወቅ ፍላጐት የነበራቸው ምእመናን አባቴን ማብራሪያ በመጠየቅ፤ ወደ መገናኛ ብዙሃን ሰልክ በመደወልና በግምባር በመቅረብ የተቃውሞም የድጋፍም ሃሳብና አስተያየት ያቀርቡ ነበረ፡፡ አባቴ ያየውን ራእይ ይፋ ማድረጉን አስመልክቶ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. የወጣው "መብሩክ" ጋዜጣ ሁለት የሃይማኖት አባቶች አነጋግሮ ያገኘውን መረጃ ለአንባብያን አቅርቦ ነበረ፡፡ ይኸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

"በግንባር የተገናኘናቸው ሁለት አባቶች በተናጠል እንደገለጡልን ከሆነ መጠራጠር አይገባም፡፡ አያሌው ዕድሜ ልኩን እግዚአብሔርን ሲያገለግል የኖረ፤ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፤ ፍጹም ከልቡ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ልበ ብርሃን ሰው ቀርቶ እጥብቆ አምላኩን የሚማጸን ፍጡር እንኳ ከፈጣሪው መልስ ማግኘት ይችላል፡፡ ጥርጣሬያችንን እናስወግድ፡፡ የጊዜው ጉዳይ አላመች እለ እንጂ በእባትነት በክብር መቀመጥና በእቋራጭ አምላክን ለመማጸን መንገድ በሆነን ነበር" በማለት አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡ ሌላ ታዋቂ አባትና ሊቀ ጳጳስ ደግሞ "እለቃ አያሌው እኛም ሁላችን

የምናምንባቸው፣ አምላካቸውን ሌት ተቀን በጸሎት የሚማጸኑ እኔም ሌላውም ለሃይማኖቱ ቀናዒ ለመሆናቸው የምናውቃቸው ናቸው፡፡ ነገ አፈር የሚጠብቃቸውና እንደ እሳቸው ያለ ታላቅ ሰው ራዕይ ሳያዩ አይቻለሁ ለማለት የማይደፍሩ ጥብቅና ድንቅ ሰው መሆናቸውን ማንም የቤተክርስቲያኒቱ አመራር አባል ያውቃል፡፡ ያምንባቸዋልም፡፡" ሲል ጋዜጣው የነበረውን ሁኔታ ገልጦታል፡፡



# ሩጫዬንም ጨርሻለሁ

ነባሩ የሊቃውንት ጉባኤ ከተበተነና የጉባዔው ሰብሳቢ የበረው አባቴ ከቤተ ክህነት ከታገደ በኋላ ከሚያዝያ ፳፱ እስከ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ተደረገ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ በቤተ ክርስቲያን ስም ተሰይመው እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ የተሾሙ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ሳይቀር ለቤተ ክርስቲያን ተጠሪ መሆናቸው ቀርቶ ለፓትሪያርኩ ተጠሪዎች እንዲሆኑ ተወሰነ፡፡ ይኸውም ሚያዚያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.ተፈርሞ ጸድቆ በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት ለሚመለከታቸው ሁሉ ተላለፈ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እስከዚያ ዕለት ድረስ ቤተ ክርስቲያን ስትሠራባቸው የኖሩት ሕጎችና ደንቦች ሁሉ መሻሻላቸውን የሚገልጽ አንቀጽ በአዲሱ ሕግ ውስጥ ተካተተ፡፡ ለዘመናት ጸንቶ በኖረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት አንጻር ሲታይ የእምነቱን ተከታዮች ከእግዚአብሔር እጅ አውጥቶ በፓትሪያርኩ አምባገነናዊ አመራር ሥር ለማንበርከክ ሆን ተብሎ የጸደቀው ይህ አዲስ ሕግ የአባቴ ቀጣይ እርምጃ ወደ ቃለ ግዝት እንዲረማመድ ዋነኛ ምክንያት ሆነ፡፡

ሚያዚያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ጸድቆ በወጣው "ሕገ ቤተ ክርስቲያን" ላይ ከሰፈሩት አናቅጽ ውስጥ ከዚህ በታች የሰፈሩትን ለአብነት አውጥተን ብንመለከት የጉዳዩን ክብደት ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

ሀ/ በምዕራፍ ፫ አንቀጽ ፭ ላይ የቅዱስ ሲኖዶስን ሥልጣንና ተግባር በሚያትተው ክፍል ተራ ቁጥር አንድ ላይ "ቅዱስ ሲኖዶስ <u>በፓትሪያርኩ አመራር ሰጪነትና ሰብሳቢነት</u> የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡"

ለ/ በምዕራፍ ፭ አንቀጽ ፲፬ ላይ የፓትሪያርኩን ከማዕረግ መውረድ አስመልክቶ በሠፈረው ሕግ " ፓትሪያርኩ የተዋህዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ ማዕረጉን

የሚያጉድፍ ሆኖ መገኘቱ በተጨባጭ ማስረጃ ሲረጋገጥ በምልዓተ ጉባኤ ያለ አንዳች የሃሳብ ልዩነት በቅዱስ ሲኖዶስ ከተጠና በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ከማዕረጉ ይወርዳል፡፡"

ሐ/ ምዕራፍ ፰ አንቀጽ ፳፫ "የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ የቅዱስ ሲኖዶሱ አባልና ጸሐፊ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ይሆናል፡፡"

መ/ምዕራፍ ፱ አንቀጽ ፳፫ "ከቅ/ሲኖዶሱ አባላት መካከል በቅዱስ ፓትርያርኩ አቅራቢነት ሦስት ዕጩዎች ተወዳድረው በቅ/ሲኖዶሱ ምልዓተ ጉባዔ የተመረጠው የመንበረ ፓትርያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማል፡፡

ሠ/ ምዕራፍ ፲፯ እንቀጽ ፴፫ "ከአሁን በፊት በቅዱስ ሲኖዶስ ወጥተው የነበሩ ሕጐች በዚህ ሕግ ተሻሽለዋል፡፡" የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

በወቅቱ ሕጉ በአምባገነናዊ ሒና መጽደቁንና የጳጳሳቱ የአቋም ጽናትም ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ፍንጮች ነበሩ፡፡ አንዱና ዋናው ሕጉን ካረቀቁትና ካጸደቁት ጳጳሳት መካከል አንዱ የነበሩት አባ ገብርኤል ለፓትርያርኩ ያቀረቡት አቤቱታነው፡፡

የሲቀ ጳጳሱ አቤቱታ፤ "የጸደቀው የሲኖዶስ ሕግ ምዕራፍ ፰ አንቀጽ ፳፫ ላይ ያለው የቅዱስ ሲኖዶስን መብት የገፈፈ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሥልጣንየተጋፋ ስርዋጽ ሕግ በምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሰረዝና ቅዱስነትዎ በእጅ ያደረጉትን የሲኖዶስ ሥልጣን ለሲኖዶስ እንዲመልሱ፡፡" [61]ይላል፡፡በመሻሻል ፋንታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ የሄደው የቀኖናና የሥርዓት ጥሰት አቡኑን ዕረፍት ነሣው፡፡ ይህንን ጉዳይ አጥብቆ ከመቃወሙ በላይ ግለሰቦች ራሳቸውን ከመንፈስ ቅዱስ በላይ በማስቀመጥ የፈጠሩት ያልተለመደ አቅጣጫ ውሎ አድሮ ከፍተኛ ውድቀት ከማስከተሉ በፊት ጽኑ ተቃውሞውን አሰማ፡፡

---

[61]ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.



ከተለያዩ አቅጣጫዎች በተሰነዘሩ ትችቶች ምክንያት የጠቀስነውን ሕግና ሌሎችን የቤተ ክርስቲያን ችግሮች እንዲያጣራ አጣሪ ኮሚሽን አቋቋሙ፡፡ ኮሚቴው በሁለት ክፍሎ ሪፖትር አወጣ፡፡ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. የወጣው የመጀመሪያው ሪፖርት ከታች የሠፈረውን ይመስላል፡፡

፩ኛ/ "... ያለ እንዳች የሐሳብ ልዩነት..." የሚለው ኃይለ ቃል በአሁኑ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የተጨመረና ፍትሀዊና ዲሞክራሲያዊ አሠራርን የሚጋፋ፤ ለውሳኔ አሰጣጥና ውጤት መገኘት እንቅፋት የሆነ ይዘት ማካተቱን የሚያመለክት ስለሆነ ቅሬታው በአግባቡ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

፪ኛ/ "... በፓትርያርኩ አመራር ስሆኑት ..."የሚለው ኃይለ ቃል በአሁኑ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የተጨመረና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ አካል ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑ ቀርቶ በቅዱስ ፓትርያርኩ አመራር ሥር የሚገለጽ የበታች አካል እንደሆነ አመልክቶ ለፓትርያርኩ ከሰብሳቢነት ያለፈ ሚና በመስጠቱና የበላይነትን በማጉናጸፉ ከዚህ አንጻር የቀረበው ቅሬታ አግባብነት ያለው መሆኑን ኮሚቴው እምኖበታል፡፡

፫ኛ/ "...ተጠሪነቱ ለቅዱስ ፓትርያርኩ ይሆናል..."የሚለው ኃይለ ቃል በአሁኑ ሕገ ቤተ ክርስቲያን የተጨመረ መሆኑና የቅዱስ ሲኖዶስ ተግባራት በተሟላ መልኩ የሚስተናገድበትና የሚገለጽበት ጠንካራ ጽ/ቤት ያልተደራጀበት መሆኑን እንደ ቅሬታው አቀራረብ መፈጸሙን የሚያመለክት ስለሆነ ቅሬታው በአግባቡ የቀረበ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

፬ኛ/ የቅዱስ ሲኖዶስን ዋና ጸሐፊና የጠቅላይ ቤተ ክህነቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ እጩዎች አስመልክቶ "...በቅዱስ ፓትርያርኩ ሁለት ሦስት እጩዎች አቅራቢነት..."ያለውን በተመለከተ በአዲሱ ሕገ ቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ ኃይለ ቃሎች መሆናቸውንና ጉባኤው እየተቃወመ የተከተቱና አለአግባብ የጸደቁ ተብለው የሚጠቀሱ ዋና ዋና የቅሬታና የውዝግብ ነጥቦች በመሆናቸው እንደገና የሚረቀቀው ሕገ

ቤተ ክርስቲያን በግልጽና በዲሞክራሲያዊ ውይይት ተመርምረው ተገቢውን ውሳኔ ቢያገኙ፡፡ የሚሉ ትችቶችንና አስተያየቶችን አካቷል፡፡

የሲኖዶሱን ሥልጣን ሽሮ ፓትርያርኩን በመንፈስ ቅዱስ ቦታ እንዲሰየሙ የሚያደርግ አዲስ ሕግ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. ሲወጣ ጉዳዩ ቀኖና ቤተክርስቲያንን የጣሰ በመሆኑ ለአባቱ እጅግ አሳዛኝና አስደንጋጭ ክስተት ነበረ፡፡

ከፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ሹመት በኋላ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሄደውን የቀኖናና የሥርዓት መዛባት ገና ከጅምሩ ቢከላከልም፣ ቢመክርም፣ ቢገሥጽም ሰሚ በማጣቱና ይልቁንም የሰየላቸው አምባገነናዊ እርምጃዎች እየተባባሱ በመምጣታቸውና ብዙ ተረማምደው ወደ ፈላጭ ቆራጭነት ሲሸጋገሩ ሲያይ ስለ ኃያሉ አምላክ ስለ እግዚአብሔር ክብር የሚቀናው አባቱ ዝም ብሎ ለማለፍ አልቻለም፡፡

አባቱ ሰሚ በማጣቱ ምክንያት ጥቅምት ፲፯ ና ህዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፯ዓ.ም. ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀረባቸው አቤቱታዎች መንፈሳዊ ገጽታቸው ችላ ተብሎ የቅሬታ አስወጋጅና ቅሬታ ኮሚቴ በተባለው ቡድን ተብጠልጥለዋል፡፡ ኮሚቴው በሌለው ሥልጣን አባቱ ከሥልጣነ ክህነት እንዲሻርና አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲወሰድበት ሲኖዶሱን ጠይቋል፡፡ ይህ ሁሉ መገፋት ቢፈጸምበትም ተጨማሪ ጥፋቶች ሲሰሩ ችላ ለማለት አልፈቀደም፡፡ ይልቁንም በብሔራዊ መብቱና በሲቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢነቱ ምክንያት በነበረው ከፍተኛ ኃላፊነትና ሥልጣን ምክንያት ያነሣውን ጥያቄ አጥብቆ ገፋበት እንጂ ወደ ኋላ አልተመለሰም፡፡ የሕጉ መውጣት ደግሞ ቀደም ብሎ ያነሣቸውን ጥያቄዎች ሁሉ አጠንክሮ እንዲገፋባቸውና ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ክብርና ስለ ቀናች እምነቱ የሚፈለገውን ሁሉ መሥዋዕትነት ለመክፈል ቆርጦ እንዲነሣ ገፋፋው፡፡

ማቁን ጨርቁን ማለት የማይጠበቅባቸው ፣ የልጆችና የትዳር ኃላፊነትና ጫና የማያስጋቸው፣"ዓለምን ንቀን ተከተልንህ" በማለት የመነኰሱ፣



በቁጥር ከ ሠላሳ በላይ የሆኑ ጳጳሳትን ያስፈራና ጸጥ ረጭ የሰኘ የፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ሥልጣን አባቱን አላስፈራውም ነበር፡፡ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት መንፈስ እግዚአብሔር ያመለከተውን ሲናገር እንዳሰው ሁሉ፤ ከፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ግርማና ሞገስ የበለጠ የሚያስፈራው፣ የሚያንቀጠቅጠው፣ እውነትንም ደፍሮ እንዲናገር የሚያስገድደው፤ የሰማያዊ ንጉሥና ካህን የኢየሱስ ክርስቶስ ግርማና ሞገስ በዓይነ ልቡናው ፊት ተዘርግ ይታየው ነበረ፡፡ በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ራሳቸውን ወደ ጣዖትነት ካሳደጉት ከአባ ጳውሎስ እንዲለዩና በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንተው እንዲቆሙ ጠየቀ፡፡ "አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፡፡ ከተቀበላችሁት ውጪ የሆነውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተወገዘ ይሁን፡፡ " (ገላ ፩፡፰-፱) የሚለውን ቃለ እግዚአብሔርና የቤተ ክርስቲያንን ህግና ሥርዓት መሠረት በማድረግ የመጀመሪያውን ቃለ ግዝት በአባ ጳውሎስና በእሳቸው በሚመራው ሲኖዶስ ላይ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት አስተላለፈ፡፡ ቃለ ውግዘቱም ከዚህ በታች የሠፈረው ነው፡፡

> *"ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር ሥራችንን ይባርክልን እላለሁ። በመቀጠልም ስሜቱን እንዲ መቆጣጠር እስከሚያቅተኝ ድረስ አየተጨነቅሁ በቃለ ጉባኤ ተባዝቶ በጽሕፈት ቤቱ በኩል ለአስፈላጊው እንዲደርስ በተደረገውና ከሚያዝያ ፳፪ እስከ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በሥራ ላይ የነበረው የጳጳሳትና የሊቃነ ጳጳሳት ስብሰባ ሲኖዶስ ጉባኤ ቤተ ክርስቲያን «ሕገ ቤተ ክርስቲያን" ብሎ ስላስተላለፈው ሕግ ያለኝን ሐሳብና ድምፅ ለመላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባሎች በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ለሚኖሩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም አስተላልፋለሁ። በእግዚአብሔር ስም አስማለሁ።*
>
> *፩ኛ፤ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ቤተ ክርስቲያን የምትመራው ወይም አመራር የምትቀበል ከእሱ ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከሰው አይደለም። ይሀንንም ራሱ*

ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "እስከ ዓለም ፍጻሜ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፤" ያለውን ቃሉን ሲያስተላልፍ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትእዛዝ፤ "ሂዱ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አስተምሩ፤" የሚል ነው።

ይህንንም መልእክት በሚፈጽሙበት ጊዜ ማን የሚመራቸው ማን እንደ ሆነ ሲያስረዳ፤ "መንፈስ ቅዱስ ይመጣል፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችሁአል፤" ብሎአቸዋል። (ማቴ፤ ም ፳፰፥ ቁ ፲፱ - ፳። ዮሐ፤ ም ፲፮፥ ቁ ፲፫።) አመራሩም ከሙሴ፥ ከኢያሱ የተለየ በውስጣቸው አድሮ የሚመራቸው መሆኑን፥ ዓለም የማያውቀው እነሱ የሚያውቁት የእውነት መንፈስ መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬ ቁጥር ፲፮-፲፯ በተጻፈ ቃሉ ገልጾ ልኳቸዋል።

እንግዲህ እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲጠብቁ ጳጳሳትን የሚሾም፥ ጉባኤያቸውን የሚመራም እሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተዋሕዶ ሃይማኖት ትምህርት ይህ ነው። ሰው ጉባኤ ቤተ ክርስቲያንን አይመራም። ግን በኋላ ዘመን ራሱን እንደ እግዚአብሔር የሚቈጥር፥ እንደ እሱ ነኝ ብሎ መሥራት የሚያምረው በቤተ እግዚአብሔር የሚኖር ትዕቢተኛ እንደሚመጣ ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሮአል። (፪ ተሰ፤ ም ፪፥ ቁ ፬።) ይህ ካልሆነ በስተቀር በቤተ እግዚአብሔር አመራር ሰጪ እኔ ነኝ ብሎ የሚናገር ወይም እሱ ነው ተብሎ የሚነገርለት ማንም የለም። ሐዋርያት ራሳቸውም በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተጠሩ፥ በወንጌል ስብከት እንደ ተላኩ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሮች፥ አገልጋዮች፥ መልእክተኞች እንደ ሆኑ ተናገሩ እንጂ፤ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማኅበር እንደ ሆነች አስተማሩ እንጂ እነሱ ጌቶች፥ መሪዎች፥ አመራር ሰጪዎች እንደ ሆኑ፥ ቤተ ክርስቲያንም የእነሱ ተጠሪ እንደ ሆነች አልተናገሩም፤ አልጻፉም።



የተፈጸመው አገልግሎት በጠቅላላ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደ ተፈጸመ፥ እንደሚፈጸም፤ የተደረገ በደል ቢኖር ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደ ተፈጸመ ጻፉ፤ ተናገሩ። ሐናንያ የተባለው ሰው የመጀመሪያዪቱን ቤተ ክርስቲያን አቋምና አርምጃ በተጠራጠረና በተፈታተነ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ፤ "መንፈስ ቅዱስን ታታልለው ዘንድ እንዲህ በልብህ ሰይጣን ሞላን? ወይስ እንዴት ሞላ፤" ብሎ ገሠጸው እንጂ የእኔን ቃል፥ የእኔን መሪነት ተላለፍክ ብሎ አልገሠጸውም።

እንዲሁም፤ "ሲጸሙና ሲጸልዩ ሳውልንና በርናባስን እኔ ለመረጥኩላቸው ሥራ ለዩልኝ ብሎ መንፈስ ቅዱስ አዘዛቸው፤" ይላል እንጂ ሰው ለመረጣቸው ሥራ አይልም። እንግዲህ፤ "ሰማይና ምድር

የሚያልፉ ቢሆንም እንኳ ቃሌ አያልፍም፤" ያለ አምላክ የመሠረተላት፥ የሠራላት ሕግ ምን ጊዜም የማያልፍ መሆኑ ቀጥተኛ እውነት ነው። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ የሚመራ በመንፈስ ቅዱስ መሆኑን፥ ቅዱስ ያሰኘውን ቅድስናውን ያገኘው፥ የሚያገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ታምናለች። ሥራዋንም በዚሁ እምነት ስታከናውን ኖራለች፤ ታከናውናለችም።

ከፓትርያርኩ ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳት፥ ጳጳሳት፥ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ፤ "ናነብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ኅሩይ ገብር ዘእግዚአብሔር፤" "በተመረጠ በዚህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ላይ እጃችንን እንጭናለን፤" በሚል አነጋገር ከሦስት ቊጥር ባላነሱ ኤጲስ ቆጶሳት ድምፅና ተግባር ቤተ ክርስቲያን የምትሾማቸው ሁሉ ተጠሪነታቸው የቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ የአንድ ሰው አይደለም። ሁሉም ይህን ያውቃሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ሐዋርያውም፤ "ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ ጳጳሳት አድርጎ የሾማችሁ እናንተ ለመንጋውና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤" ወይም፤

"የተሾማችሁባቸውን መንጋዎችን ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤" ብሎ የተናገረ ስለዚህ ነው። (የሐ፤ ሥራ ም ፳፥ ቍ ፳፰።)

፪ኛ፤ ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስኩት ቋሚ መመሪያ ሲሆን ልዩ ልዩ መናፍቃን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተነሡበት ጊዜ ሁሉ ጉባኤ ጳጳሳት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እየተሰበሰቡ ቤተ ክርስቲያንን ከስሕተት፥ ከኑፋቄ ሲጠብቁ ኖረዋል። በኋላ ግን ከቤተ ክርስቲያን ክብር እየሸሹ፥ ወደ ዓለማዊ ክብር እየተጠጉ፥የእግዚአብሔርን ኃይልና ሥልጣን መከታ አድርገው መሥራት ሲገባቸው በመንግሥታዊ የፖለቲካ ኃይልና ሥልጣን መጠቀም የፈለጉ መለካውያን ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን ላይ መከፋፈልን ስለ ፈጠሩ በምድር ላይ ዳግማዊ ክርስቶስ የሚባል መሪ አበጁ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን በዚህ የፈተና ጊዜ በሃላፊዎችና በአለተዋይ ሊቃውንቶቿ አስተዋይነት፥ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጸንታ ኖረች። ለሰው አልተንበረከከችም። ይህም በኢትዮጵያ አስተዳደር መንግሥት የሰውጥ ጊዜ እስከ መጣበት እስከ ፲፱፻፷፮ ዓመተ ምሕረት ድረስ ጸንቶ ኖሯል። ከዚያ ወዲህ ግን የሥጋዊው ቍስል ወደ መንፈሳዊው ተጋብቶ ይመስላል ኢትዮጵያ በቍስል ላይ ቍስል ተጨምሮባት በሥጋዊ አስተዳደር ኮሚዩኒዝም ያመጣበት በሽታ መንፈሳዊ አቋሟንም ጎድቶታል። በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ከደረሱት ዋና ዋና ችግሮች፤

ሀ/የሃይማኖት ሕፀፅና የሥርዓት መበላሸት፤

ለ/በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ—አደግ የሆኑ መናፍቃን መፈልፈልና የኑፋቄ መጻሕፍትን ማብዛት፤

ሐ/ ፓትርያርኮቿ ወደ ራስ ትምክህት፥ ወደ እብሪትና ወደ ትዕቢት በመተላለፋቸው ሲኖዶሱን የግል



ግዛታቸው ማድረጋቸው፥ በገዛ ሥልጣናቸው ሲኖዶስ እየፈረሱ ሲኖዶስ መሰየማቸው፥ በመንግሥት የሥልጣን ድጋፍ ወደ ማዕረግ መውጣታቸው ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በአምስተኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመን የታየው ደግሞ በውጭ ያዩት ዳግማዊ ክርስቶስ ተብሎ መሰየምና በፓትርያርክነት ቢመረጡ በአምላክ ፈንታ ሆኖ መንፈስ ቅዱስን መጋፋት፥ ዳኝነቱን መርገጥ ሆኗል። ይህም በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የማይጠገን ስብራት፥ የማይድን ቍስል ሆኖባታል።

፫ኛ/ እኔ በእነዚህ ፳፱ ና ፳፫ ዓመታት አቤቱታዬን ሳሰማ ኖሬአለሁ። ዕድል ሆኖና ዛሬም እጮሃለሁ። ድምጼ ግን በውሃ ውስጥ እንደሚናገር ሰው ተሰሚነት አላገኘም። ግን በእግዚአብሔር ላይ አሁንም ተስፋ አልቆረጥም። እንደገና እጮሃለሁ፤ እንደገና አቤት እላለሁ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ፍርሃታቸውን ከልባቸው አውጥተው ጥለው ለቤተ ክርስቲያናቸው፥ ለሀገራቸው፥ ለሃይማኖታቸው፥ ለክብራቸው መቆም እስከ ቻሉ ድረስ አቤቱታዬን አሰማለሁ።

ከዚህ በላይ የዘረዘርኩት እንደ መቅድም ያህል ሲሆን ፍሬ ነገሩ የሚከተለው ነው። እንደሚታወቀው ዘንድሮ በ፲፱፻፺፰ የተደረጉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠቅላላ ስብሰባና የሊቃነ ጳጳሳት ስብሰባ አንደኛ በጥቅምት፥ ሁለተኛ በሚያዝያና በግንቦት መገናኛ ከሚያዝያ ፳፱ እስከ ግንቦት ፯ የተደረጉ ሲሆኑ ሁለቱም ጊዜዎች ሸር የተሞላባቸው ነበሩ። ይህንንም እንደሚከተለው እገልጻለሁ።

ሀ/ በቤተ ክርስቲያን የደረሱት ልዩ ልዩ ችግሮች ሁሉ በሲኖዶስ ተመክሮባቸው እንዲወገዱና እርምጃቸውም እንዲገታ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጥቅምትና ኅዳር ወር ለሲኖዶሱ ማመልከቻ ስጽፍ

መልእክቱ በጌታቹ በእምነቱ ትእዛዝ የተደረገ መሆኑን ገልጠው በአፈጻጸሙ ቸልተኛነት እንዳይታይበት ሲኖዶሱን በሾሙ በመንፈስ ቅዱስ ዳኝነት ተማጽኜ አቤቱታዬ የእኔ ብቻ ሳይሆን በዐጸደ ሥጋና በዐጸደ ነፍስ ያሉ የኦርቶዶክሳውያን አበውና ምእመናን አቤቱታ መሆኑን ገልጠው ነበር ያቀረቡት። ነገር ግን የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ አባ ገሪማና ፓትሪያርኩ ሐሳባቸው እስከ አሁን በቤተ ክርስቲያን የኖረውን የመንፈስ ቅዱስን መሪነት ሽረው የራሳቸውን ማያታዊ መሪነት ለመተካት ኖሮ በጥቅምት ወር ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት በተደረገው አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ያቀረቡትን አቤቱታ ጭምር ሳይቀበሉ ከመቅረታቸውም በላይ የመንፈስ ቅዱስን ዳኝነት፥ የሲኖዶሱን ሥልጣን ለግል አድመኞቻቸው ኮሚቴ አሳልፈው በመስጠትና በሱ ውሳኔ ተደግፈው የንቀቄ መጽሐፍ ማውጣታቸውና መበተናቸው እንቦ ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ አፍርሰዋል።

ለ/ ይህ በዚህ እንዳለ ሲኖዶሱ ተሰብስቦ ጉዳዩን እንዲያይ በግል ማመልከቻ፤ በነጻ ፕሬሱ በኩልም ተቃውሞዬን በማሰማት ላይ እያለሁ ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓመተ ምሕረት የቅሬታ አስወጋጅና የሰላም ኮሚቴ በሚሉት የግል ኮሚቴያቸው ድጋፍ እኔን ካባረሩ በኋላ ከሚያዚያ ፳፱ እስከ ግንቦት ፮ ባደረጉት በአፈና የሲኖዶስ ስብሰባ ሕግ አስወጥተው በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ ራሳቸው ፓትሪያርኩ ሲኖዶሱ ወንጌልን ለሚሰብክበት፥ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ለሚያስተምርበት ጉዞ አመራር ሰጪ (ጣዖት) ወደ መሆን አድገዋል።

በቤተ ክርስቲያን ስም ተሰይመው እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ሊያገለግሉ የተሾሙ ሊጳስ ቆጳሳት፥ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ሳይቀር ለቤተ ክርስቲያን ተጠሪ መሆናቸው ቀርቶ ለፓትሪያርኩ ተጠሪዎች እንዲሆኑ ሲያደርጉ በዚያ ሚያዚያ ፴ ቀን ተፈርሞ ጸድቋል በተባለውና በጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት ለሚመለከተው ሁሉ እንዲተላለፍ



የቃለ ጉባኤ ትእዛዝ በተሰጠበት ሕግ፤ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን በትሠራባቸው የኖሩት ሕጎችና ደንቦች ሁሉ በዚህ ሕግ "ተሻሽለው" ከስፍራቸው ሲወገዱ፥ አባ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ የቤተ ክርስቲያኒቱን የአመራር ሰጪነት በታ ሲይዙ በቤተ ክርስቲያን ላይ የአምልኮ ጣዖት ዐዋጅ ታውጀቢታል። ፓትሪያርኩ በሾማቸው በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ላይ በፈጸሙት ተግባር ታላቅ በደል ፈጽመዋል። ከሳቸው ጋር ቃላቸውን ለማጽደቅ፥ ምኞታቸውን ለሟሟላት በሕጉ ላይ ፈርመዋል ተብሎ ስማቸው የተመዘገበላቸው ፴፬፡ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳትም እንደ ተባለው አድርገውት ከሆነ ለተፈጸመው በደል ተባባሪዎች ናቸው። ይህም እጅግ የሚያሳዝን ነው።

የሚገርመው ደግሞ በዚሁ ሕግ በአንቀጽ ፲፩፤ «ፓትሪያርኩ የተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፥ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ፥ ማዕረጉን የሚያጎድፍ ሆኖ መገኘቱ በተጨባጭ ማስረጃ ሲረጋገጥ በምልአተ ጉባዔ ያለአንዳች የሐሳብ ልዩነት በቅዱስ ሲኖዶስ ከተጠና በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ከማዕረጉ ይወርዳል፤» የሚል ቃል አስፍሮ ሲኖዶሱን በአፈና ልዩ ሥልጣን ተጠቅመውና እንደ ሌለ አድርገው ካሳዩ በኋላ፤ «የንቀቄ መጻሕፍት በማሳተም የተዋሕዶ ሃይማኖትን አፋልሰዋል፤ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ሳይጠብቁ ቤተ ክርስቲያን ከምታወግዛቸው ጋር የጸሎት ቅዳሴና የማዕድ ተሳትፎ አድርገዋል፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከምታወግዘው ፓፓ በራሴ ተቀብለዋል፤» እያልን እየተቃወምን ለተቃውሟችንም ተጨባጭ ማስረጃ እያቀረብን፤ እሳቸውም ይህንን ሳይቃወሙ ይህ እንዳይቀጥል በሥልጣናቸው ተጠቅመው ኦርቶዶክሳዊውን የሊቃውንት ጉባኤ ሲያፈርሱ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ በመስጠት ፈንታ እንደገና በሕግ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስፍራ ተተክተው ለሲኖዶሱ ሥልጣንና ተግባር አመራር ሰጪ ይሆናሉ፤ የሲኖዶሱ አባሎች ሁሉ ለፓትሪያርኩ ተጠሪ ይሆናሉ፤ ሲል የወጣው አዋጅ አፈጻጸም ነው። ይህ ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ

የታወጀው ሕግ፤ «እስመ ሜጥዋ ለዐመፃ ኅዕሊክ፤» «ዐመጽን ወደ አንተ መለሷት፤» ተብሎ እንደ ተጻፈ ቤተ ክርስቲያንን መካነ ጣዖት፥ ምእመናንን መምለክያነ ጣዖት የሚያሰኝ ስለ ሆነ ምእመናን ሁሉ በሙሉ ድምፅ እንድትቃወሙት በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ስም አጠይቃለሁ።

ሐ/ ከአሁን ጀምሮ ማለት ይህ ቃል ከተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቃልና እጅ፥ በሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ በአቡነ ገሪማ ቃልና እጅ፥ ይህን አሁን የተጻፈውን ሕግ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ብለው አጽድቀው በተባባሪነት አሳልፈዋል የተባሉ ጳጳሳትና ሊቃነ ጳጳሳት ሁሉ እውነት ሆኖ ከተገኘ የበደሉ ተባባሪዎች ናቸውና በነሱ ቃልና እጅ በራሴ እንዳትቀበሉ፥ እንዳትናዘዙ፤ ለማቸውን በጸሎተ ቅዳሴ የሚጠሩ አለቆች፥ ቀሳውስት፥ ካህናት ካሉም የአምልኮተ ጣዖት አራማጅ ናቸውና ተጠንቀቁባቸው፤ ምክር ስጡቸው፤ እንቢ ካሉም ተለዩዋቸው። እንዲሁም ሐምሌ ፳ ወይም ፯ ቀን ይከበራል ተብሎ ሽርጉድ የሚባልለት በዓለ ሢመት የእርግን የወርቅ ጥጃ መታሰቢያ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ሊከበር የማይገባው ስለ ሆነ በዓሉ ከመድረሱ በፊት የሲኖዶሱ አባላት በአስቸኳይ ተሰብስበው ሕጉን ካልሻሩና በጣዖትነት የተሰየሙትን አቡነ ጳውሎስን ከሥልጣናቸው ካላነሡ ምእመናን ይህንን በዓል እንዳታከብሩ ለቤተ ክርስቲያን ደሙን ባፈሰሰ አምላክ ስም፥ ቤተ ክርስቲያንን በሚመራና በሚጠብቅ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥያቄዬን አስተላልፋለሁ። ምናልባት የሕጉን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት የተሳነው፥ ግን በልዩ ልዩ ዲጋፊዎቻቸው ተጭበርብሮ በቻሌታ የሚመለከተው፤ ከዚያም ዐልፎ በሥልጣናቸው እየተመኩ ለቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ጆሯችንን አንሰጥም ብለው ይህን በደል ያደረሱትን ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስን፥ በሦስት የሹመት ስም የሚንቀባረሩትን አባ ገሪማን፥ ለነሱ ድጋፍ የሚሰጡትንም ሁሉ፤ ጌታዬ አምላኬ፤ «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤» ሲል በሰጠው ቃል በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን፤ በጴጥሮስ፥



በጳውሎስ፥ በማርቆስ፥ በቄርሎስ፥ በባስልዮስ፥ በቴዎፍሎስ፥ በተክለ ሃይማኖት ዘደብረ ሊባኖስ ቃል፤ ኃጥእ ደካማም በምሆን በእኔም በቀሲስ ወልደ ጊዮርጊስ ቃል አውግዤአለሁ። ይህን ሕግ የተቀበሉና ከሥራ ላይ ያዋሉ ሁሉ እንደ አርዮስ፥ እንደ መቅዶንዮስ፥ እንደ ንስጥሮስ፥ እንደ ፍላቢያኖስ፤ እንደ ኬልቄዶን ጉባኤና ተከታዮቹ እሱራን፥ ውጉዛን ይሁኑ። በማይፈታው በእግዚአብሔር ሥልጣን አስሬአለሁ።

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን አሜን።

ማስጠንቀቂያ፤ አምላኬ ሂድ ተናገር ያለኝን ትእዛዝ ለእናንተ አድርሻለሁ። ኃጢአቴንም ጨርሻለሁ። ከእንግዲህ ተጠያቂነቱ የእናንተ የምእመናንና ታሪክ ተጠያቂ ያደረገው የመንግሥት ነው። ለዚህም ምስክሬ ራሱ እግዚአብሔር፥ ቅዱሳን መላእክት፥ ሰማይና ምድር ናቸው።» አለቃ አያሌው ታምሩ ዘዲማ ጊዮርጊስ።

ከላይ የሠፈረውን ቃለ ውግዘት በተለከተ በርካታ ምእመናን ግራ የተጋቡበትንና ግልጽ ያልሆነላቸውን ለመረዳት ጥያቄዎችን ያቀርቡ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ኢትኦጵ የተባለው ጋዜጣ የአባቴን ማብራሪያ በመጠየቅ ባቀረበው ጽሑፍ ስለውግዘት ምንነት ምእመናን ማወቅ የሚገባቸውን ትምህርት አስተላልፏል፡፡

በአባቴ ትምህርት መሠረት ውግዘት እንደተራ ነገር አይወረወርም፡፡ ተጠንቶ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ነው የሚሰነዘረው፡፡ ውግዘት ማለት ሰይፍ ነው፡፡ በቅዱስ ጳውሎስ ቃል መሠረት የእግዚአብሔር ቃል ጽኑና ኃያል ነው፡፡ ሁለት ልሳን ካለው ሰይፍ ይበልጥ ስለት ያለው ነው፡፡ ነፍስን ከሥጋ አጥንትን ከጅማት የሚለይ ሐሳብና ልብን ሳይቀር የሚመረምር ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ቃል"ብሎ የተጠቀሰውም ውግዝትን ነው፡፡ በዚህ መሠረት፤

፩ኛ/ ውግዘት መናፍቃንን ከርኩሳን የሚለይ "አንተ ርኩስ ውጣ" ብሎ የሚገለጽና ከስዎች የሚያርቅ ነው፡፡

፪/መናፍቃንን ከማሐይምናን የሚለይ፣ እንመለስም እምቢ ያሉትን የሚቀጣ ነው፡፡ ሁሉ ሌላውን እንዳይበክሉ በውግዘት ይለያሉ፡፡

አባቴ እንዳስተማረው ፤ በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ዝንጉርጉር ለምጽ የነበረበት ሰው ብዙ ሕዝብ በሚያርፍበት መካከል አይኖርም፡፡ ሙሉ ለምጽ ከሆነ ግን አይከለከልም፡፡ ምክንያቱም ሙሉ ለምጽ ከሆነ ሁሉም ያውቀዋል፡፡ ዝንጉርጉር ከሆነ ግን የማያውቅ ስለሚጠጋውና ስለሚጋባ በዚሁ ምክንያት ዝንጉርጉር ለምጽ ያለው በህዝብ መካከል እንዳይኖር ተወስኗል፡፡ ይህም የመናፍቃን ምሳሌ ነው፡፡ አባቴ ለኢትኦጵ ጋዜጣ እንደገለጠው፤

"...የለየለት የማያምን ከሆነ አብሮ መኖር ይችላል፡፡ ችግር የሌለ መስሎ አያስትም፡፡ እስላም ክርስቲያን አብረው መኖር ይችላሉ፡፡ ሃይማኖታቸው የተለያየ ስለሆነ፡፡ ግን በክርስቲያን መካከል ያለ ልዩነት ይዘው እየተሽሎከሎኩ ቤተ ክርስቲያንን የሚለውጡ፣ የምእመናንን ትምህርት የሚያናውጡና የሚበርዙ ሆነው ከተገኙ በውግዘት ይለያሉ፡፡ ..."

በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጠው ተጨማሪ ትምህርት ልዩ ትምህርት ይዞ የሚያውከን ሰው በመጀመሪያ አንድ ሁለት ሦስት ሆኖ ምክር መስጠት ይቻላል፡፡ ይህ ሳይቻል ከቀረ ግን በጉባኤ ለምእመናን ተነግሮ ስህተቱ፣ በደሉ፣ ክህደቱ ታውቆ ይለያል፡፡ በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ መናፍቃን ከቤተ ክርስቲያን ወጥተዋል፡፡

ብዙውን ትተን በአጭሩ ለመጥቀስ "ወልድ በመለኮቱ ፍጡር ነው" በማለት ዛሬ "ጆሆቫ" የሚሰብከውን ስብከት ያመነጨው አርዮስ፣ "ክርስቶስ አምላክ የደረበት ሰው ነው እንጂ አምላክ አይደለም" ያለ ሳምሰጢ ጳውሎስ፣ "መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ያንሳል" ያለ



መቅደንዮስ፣ "ለክርስቶስ ሁለት አካልሁለት ባሕርይ አለው" ያለ ንስጥሮስ፣ "አንድ አካል ሁለት ባህርይ ነው" ያለ ፍላብያኖስና የሌን ሃሳብ ደግፎ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ ልዮን በጉባዔ ተወግዘው ተለይተዋል፡፡

ይህ የሆነው ኦርቶዶክሳዊት ርትዕት ሃይማኖት በቤተክርስቲያን ጸንታ እንድትኖር ነው፡፡ ከዚህ በኋላ አንዱ ወደ ሌላው ሊሄድ አይችልም በውግዘት ተገድቧል፡፡ስለ ውግዘት ጨምሮ ሲያስረዳም ፤

"...ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው፡፡ ጽኑ ነው፡፡ ሁለት ልሳን ካለው ሰይፍ የሰለጠ ነው፡፡ ነፍስን ከሥጋ፣ አጥንትን ከጅማት ሁለቱን ከልብ የሚለይ የሚመረምር ነው ሲል በተናገረለት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መናፍቃንና ተከታዮቻቸው በየጊዜው ሲለዩ ሲወገዙ ይኖራሉ፡፡ ጌታ "መጀመሪያ ራስህ ቀጥተው ሁለት ሦስት ይዘህ፤ ከዚህ በኋላ አልመለሰም ካለ ለቤተ ክርስቲያን ንገሯት፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ነግረሃት ቤተ ክርስቲያንን አልሰማም ካለ እንደ አረመኔ ይቆጠር" ሲል ማንም ሰው የቤተክርስቲያን ትምህርት ሥርዓት ሕግ መጠበቅ የማይችል ሆኖ ተመክሮ የማይመለስ ከሆነ መጀመሪያ በግል በምሥጢር በግዝት ተወግዞ ይለያል ባለው መሠረት ነው እኔ የወገዝኩት፡፡..."በማለት ተናግረዋል፡፡

## ውግዘቱን ማን ይፈታዋል?
## ልብ ያለው ልብ ይበል!

አባቴ ያሳሰፈውን ቃለ ግዝት የአንድ ሰው ወይም የጥቂት ሰዎች ጉዳይ ብቻ አድርጎ ማሰብ ትክክል አይደለም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለምን ቢባል ፤

፩ኛ) ከእውነተኛ መንፈሳዊ አባት የተላለፈ እውነተኛነት ግዝት እንጂ ወፈ ገዝት ባለመሆኑ፤

፪ኛ) አባቴ ባየው ራዕይና በነበረው ሀብተ ትንቢት መሠረትነት የተናገራቸው ሁሉ አብዛኛዎቹ የተፈጸሙ የቀሩትም ደግሞ የማይቀሩ መሆናቸውን አጥብቄ የማምን በመሆኑ፤

፫ኛ) አባቴ የሰጣቸውን ምክሮችና መመሪያዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችም ምእመናን ልብ ብለው ቢያደምጡ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና በቤተክርስቲያን ላይ እየወረደ ያለው አበሳ ማቆሚያ ሊያገኝ ይችላል ከሚል በመነሳት ነው፡፡

ስለ የጉዳዩ ጥልቀትና ክብደት በ፲፱፻፺ዎቹ ብዛት ያላቸው ወጣቶች ወደ አባቴ በመሄድ ያቀረቧቸውን ጥያቄዎችና በወቅቱ አባቴ የሰጡትን መልስ ልብ ማለት መልካም ነው በሚል እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

**ጥያቄ ፩፤ ውግዘት ማለት ምን ማለት ነው?**

መልስ፤ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ አንድ ሰው ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጪ ከሆነ እንኳን መሬ ሆኖ በምእመንነት ያለም ቢሆን ሁኑን ከተጣለፈ ይወገዛል፡፡ ሃይማኖት የተጣለፈ ብቻ አይደለም ሥርዓትም ፡፡ እንኳን ይሆን ያህል ያቤተ ክርስቲያን ያፋለሰ ቀርቶ ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር ተጣልቶ አልታረቅም ቢል እንኳ ይወገዛል፡፡ ጌታችን አንድ ሰው ቢበድል መጀመሪያ ብቻህን፤ ሁለተኛ ሰው ጨምረህ ንገረው እምቢ ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፡፡ ቤተ ክርስቲያንን እምቢ ካለ



እንደ አረመኔ እንደ ቀራጭ ይሁን ነው ያለ፡፡ ይኼ ውግዘት ነው፡፡ ከዚያ አያይዞ ሲናገርም በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፡፡ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል፡፡ ብሏል፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን መማሪያ ውግዘት ነው፡፡

**ጥያቄ ፪፤ አንድ ሰው ተወገዘ ሲባል ምን ምን ሲሰራ ነው?**

መልስ፤ ከቤተክርስቲያን ከህግ ውጪ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ካደረገ ይወገዛል፡፡ትምህርተ ሃይማኖት ካፋለሰ፤ ሥርዓት ከጣሰ፤ ሕግ ካፈረሰ፤ ሃይማኖት ካጠፋ በሰውም በእግዚአብሔርም ላይ በደል ካደረሰና ተመክሮ ተነግሮ እምቢ ካለ ይወገዛል፡፡ ማውገዝ ማለት መለየት ማለት ነው፡፡ እንኳን በመንፈሳዊ ሕይወት በሥጋዊ ሕይወትም ድሮ አባቶች እንዲህ ያደርጉ ነበር፡፡እንዲህ ባይሆን የኒቅያ፤ የቁስጥንጥንያ፤ የኤፌሶን ጉባዔዎች አያስፈልጉም ነበር እነ አርዮስ፤ እነ መቅዶንዮስ፤ እነ ንስጥሮስ ተወግዘው አይለዩም ነበር፡፡ ... ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ በሙሴ ህግ ያጠፋ ሰው በሁለት በሦስት ሰው ፊት ከተወቀሰ ይቀጣል ይላል፡፡ ግን ወልደ እግዚአብሔርን በደሙ ቃልኪዳን የተጋባና የተቀበለውን ቅድስና ያረከሰ የጸጋ መንፈስ ያዋረደ ቢኖር እንዴት አይቀጣም? ... አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ እኔ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልኖር በመንፈሴ ከእናንተ ጋር ነኝ እንዲህ ያለውን ሰው ዝም ብላችሁ መመልከት አይገባችሁም ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብስባችሁ አውግዙት፡፡ ለዩት፡፡ ለሠይጣንስጡት ነው የሚል፡፡ ቆሮ፡ም፡፩ ፡፡ እኔም ያወገዝኩት ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ነው፡፡

**ጥያቄ ፫፦ በፓትሪያርኩና በእርስዎ መካከል የተፈጠረው ችግር ስመፍታት ለምን አልተቻለም?**

መልስ፤ አይቻልምም፡፡ አልተቻለምም፡፡ ምክንያቱም እሳቸውሲመለሱ ነው የሚፈታ፡፡ ወይም ከመካከላችን ዳኛ ሲኖር ነው የሚፈታ፡፡ በመካከላችን ጉባዔ የሚጠራ ንጉሥ የለም ዛሬ፡፡ አርዮስሲወገዝ የኒቅያን ጉባዔ ቆስጠንጢኖስ፤ መቅዶንዮስ ሲወገዝ አርቃድስ፤ ንስጥሮስ ሲወገዝ

ቴዎዶስዮስ የተባሉ ነገሥታት ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያም ነገሥታቱ በነበሩበት ጊዜ በየጊዜው የተደጋገመ ጉባዔ ደርጓል፡፡በአፄ ፋሲል ጊዜ በካቶሊክና በኢትዮጵየ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማንያን መካከል ጉባዔ ተደርጐ የኢትዮጵየ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አሸ ጉባዔ አፄሁ በትረ ጊዮርጊስ ስለረቱ ካቶሊኮች መረታታቸውን አምነውተቀብለው ከአገር እንዲወጡ ተፈርዶባቸዋል፡፡ በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በቦሩ ሜዳ ጸጐችና ኦርቶዶክሳውያን ሲቃውንት እንዲከራከሩ ተደርጐ ጸጐች ስለተረቱ ተፈርዶባቸው ተቀጥተዋል፡፡ ንጉሥ ቢኖር ይህንን ጉባዔ ጠርቶ ሊፈታው ይችል ነበረ፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ንጉሠ ነገሥቱ ነበርና፡፡ ዛሬ ንጉሠ ነገሥት የለም፡፡ ያለው መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ አየገባኝም አለ፡፡ ይህንን ምክንያት አድርገው ፓትሪያርኩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ረገጡ፡፡ ክብሯን አሳደፉ፡፡

**ጥያቄ ፭፦ ፓትርያርኩ ቢያጠፉ ወይም ሃይማኖት ቢያፋልሱ እራሳቸው በሰሩት ሥራ ይቀጣሉ እንጂ፣ ካህናት አባቶች ተባባሪዎች ናቸው ተብለው ለምን ይወገዛሉ?**

**መልስ፤**

ፓትሪያርኩ ሲያጠፉ የምትሾምም የምትሽርም ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ፓትሪያርኩ እኮ አምባገነን አይደሉም፡፡ በጦር ጉልበት አይደለም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መንበር የወረሱት፡፡ በልዩ ሥልጣናቸውም አይደለም፡፡ ልዩ መብትም የላቸውም፡፡ የወራሽነት መብትም የላቸውም፡፡ተመርጠውነው የተሾሙት፡፡ ሲሾሙም ደግሞ ምስው ነው፡፡ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ሥርዓትና እምነት ሊጠብቁ ነው፡፡ ካልጠበቁ መሻር አለባቸው፡፡ ካልሻሯቸውይወቀሳሉይከሰሳሉ፡፡ አብረዋቸው ይሻራሉ፡፡



**ጥያቄ ፮፦ ቤተክርስቲያናችን ውሉጊዜ ስለ ፍቅር እያስተማረች፣ በእርስዎና በፓትርያሪኩ መካከል ለምን ፍቅር ጠፋ?**

መልስ፤በእኔና በእሳቸው መካከል አይደለም ፍቅር የጠፋው፡፡ በቤተክርስቲያንና በእሳቸው መካከል ነው፡፡ እኔና እሳቸው እሁንም አልተጣላንም፡፡ አልበደሉኝም አልበደልኳቸውም፡፡የግል ቂምየለኝም፡፡ ጸባችን በቤተክርስቲያን ምክንያት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ደግሞ መታረቅም መተባበርም አይቻልም፡፡ ሄሮድስና ጲላጦስ ጥክረውት ነበረ፡፡ አልተደረገም፡፡ በእግዚአብሔር ላይ መጥጥል፣ በእግዚአብሔር ላይ ወዳጅነት መፍጠር አይቻልም፡፡ ይሄማ ቢሆን ኖር ጌታ ለምንድን ነው "በሰው ፊት ያመነብኝን በሰማይ አባቴ ፊት አምነዋለሁ፤ በሰው ፊት ያፈረብኝን በሰማይ አባቴ አፍርበታለሁ፡፡" ለምን ይል ነበረ? ጌታ እኔ ሠይፍን እንጂ ሰላምን አላመጣሁም፡፡ አባትን ከልጁ፤ እናትን ከልጇ፣ ቤተሰብን ከቤተሰቡ ልለያይ ነው የመጣሁ ነው ያለ፡፡ ታዲያ ይህ ባይሆን ኖሮ በዓለም ምን ጸብ ይኖር ነበረ? በዓለም ምን ሰማዕታት ይገኙ ነበረ? ለምን ይሞቱ ነበር? ለምን ደማቸውን ያፈሱ ነበር? በእግዚአብሔር ላይ ውስታ መዋዋልና ፍቅር መፍጠር አይቻልም፡፡

**ጥያቄ ፯፦ ምእመኑስ፥ ለምን በቤተክርስቲያን ተገኝቶ እንዲያስቀድስ ታገዱ?**

መልስ፤እስኪ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዐስርን እዩት፡፡ "በጐቼ ቃሌን ያውቃሉ፡፡ እኔ በስማቸው እጠራቸዋለሁ፡፡ ይከተሉኛል፡፡ ሌላውን ግን አያውቁትም፤ ስለዚህ ቃሉንም አይሰሙትም፤ አይከተሉትም" ነው ያለ፡፡ ከክርስቶስ ውጪ የሆነ እረኛ የለንም፡፡ ከክርስቶስ ውጪ የሆነ ፓትሪያርክ የለንም፡፡ ከሌለን ደግሞ ምእመናንን ሊሰሙት ፣ ሊቀበሉትና ሊከተሉት አይገባም፡፡ ማንን ነው የሚያስቀድሱት? ማንን ነው የሚቀድስ? ዲያብሎስ ይቀድሳል እንዴ? አይቀድስም እኮ፡፡ ይህንን አታውቁም? ቅዱሳን መላእክት ናቸው እንጂ የሚቀድሱ ዲያብሎስ አያስቀድስም፡፡ "ቅዱስ" ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል አይጠራም፡፡ እና እንዚህ እግዚአብሔርን የካዱ መቀደስ አይችሉም፡፡ ዐላዉ ደግሞም ማስቀደስ አይቻልም፡፡ የትዳሉ ተባባሪ መሆንም አንችልም፡፡ ስለዚህ

ምእመናንን ከዚህ መታቀብ አለባቸው፡፡ ምእመናንንናቸው ወንጀለኞች እንግዲያውስ፡፡ አንደኛ ከበው እያጨበጨቡ፡፡ ሁለተኛ ሲወጡ ሲገቡ እጅ እየነሱ፣ቁጭ ብድግ እያሉ፡፡ሦስተኛ ገንዘባቸውን እየሰበሰቡ እየሰጡ ለጣዖት አምልኮ ማጠናከሪያ ያደረጓት፡፡ምእመናን ራሳቸው ናቸው ፡፡ ስምንት መቶ ሺ ብር የፈጀ መኪና የተገዛ በምእመናንን ገንዘብ ነው፡፡ ምዝበራ ነው፡፡ አንድ ሚሊዮን ተኩል የፈጀ ግብግብ የተጋበዘው ከቤተ ክርስቲያን በተፈጸመ ምዝበራ ነው፡፡ ምእመናንን እጃቸውን ቢሰበስቡ፣ የሰበካ ጉባኤ አደራውን ቢጠብቅ ኖሮ እንዲህ አይደረግም ነበር፡፡ ራሳቸው በጉባኤ እንደተናገሩት በገጠር ያሉ ድሆችአብያተ ክርስቲያናት የሚረዱበት አጥተው በሙታን ሴቶች ቀሚስ እየተቀደሰ ፤ ይህን የሚሰሙ ምእመናንን ናቸው ዝም ብለው የሚያጨበጭቡ፡፡ ደግሞስ በቤተክርስቲያን ላይ ደም እየፈሰሰ፤ ደም አፍሳሽ ቅዱስ ነው እንዴ? ደም አፍሳሽ ቅዱስ ነው? ይሄንን የአዲስ አበባ ህዝብ ዓይኑ አይቶ የለም? ሰምቶ የለም? ከዚህ ነው ቅዳሴ የሚያገኘው?

ጥያቄ ፯፦ ሰው በቤተ-ክርስቲያን ተገኝቶ እስቀድሶና ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ለምን ተከለከለ?

እኔ አልከለከልኩም፡፡ የሚያቀብላችሁ ካገኛችሁ፣ ቅዳሴ የሚቀድስ ቄስ ጳጳስ ካላችሁ እኔ አልከለከልኩም፡፡የላችሁም እንጂ፡፡

ጥያቄ ፰፦ የጌታ ሥጋ ወደሙ በካህናት አባቶች እጅ አትቀበሉ፤ የፓትርያርኩ ተባባሪዎች ናቸው ለምን ተባለ?

መልስ፤ሥልጣነ ክህነት የላቸውም እኮ ነው እያልኩ ያለሁት፡፡ የፓትርያርኩ ተባባሪ የሆነ ሁሉ ሥልጣነ ተክህኖ የለውም፡፡ ምክንያቱም ሚያዚያ ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. የወጣው ህግ ሲንዶሱ የፈረመበት ህግ እስከ ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትሰራባቸውን ደንቦችና ህጎች እናፍሮ የሚመራና ለሲኖዶሱ ተጠሪ የነበረው ፓትርያርክ በመንፈስ ቅዱስ ፈንታ መሪ እንዲሆን ፤ አመራር ሰጪ እንዲሆን ፈቅዶ ቤተ ክርስቲያንንና አባቶቿን የፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ተጠሪ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ጳጳሳትም ቀሳውስትም ራሳቸውን ሽረው



የአባ ጳውሎስ ፍጡራን ስለሆኑ ፤ አባ ጳውሎስ ደግሞ ሥልጣነ ክህነት የመስጠት መብት ስለሌላቸው አሁን ዛሬ የሚቀድሱ፣ የሚያወድሱ ካህናት ቄሶችም ጳጳሳትም የሉንም፡፡ ስለዚህ ካሏችሁ አልቃወምም፡፡

ጥያቄ ፱፦ የእናንተ የሃይማኖት አባቶች ፍቅር መጥፋት፤ ለመናፍቃን፣ በር አይከፍትም ወይ?

ጥያቄ ፲፦ ዛሬ ዛሬ መናፍቃኑ "በእነሱ በኩል ፍቅር ጠፍቷል፣ እንደምታዩአቸው አንዱ አንዱን እየወገዘ ነው ያለ" እያሉ ይሳለቁብናል። በእርሶ በኩል ይኼን እንዴት ያዩታል?

መልስ፤ፍቅር እኮ አልጠፋም፡፡ ግን በእግዚአብሔር ቀሰድ የሰም፡፡ በእግዚአብሔር እድማ የሰም፡፡ እድማ እኮ ነው፡፡ ምን አማላን? ምንም ጠብ የለንም፡፡

ጥያቄ ፲፩፦ ይኸ ውግዘት የተላለፈው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፤ ወይስ ለአዲስ አበባ ከተማ ብቻ?

መልስ፤ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ነው፡፡ በዓለም ላሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፡፡

ጥያቄ ፲፪፦የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ ወደሙ ከካህናት አባቶች እጅ አትቀበሉ ለምን ተባለ?

መልስ፤መስቀል ብቻውን መባረኪያ አይሆንም፡፡ታዲያ ለምን እንጥረዋለን፡፡ እይባርከበትም?ታዲያ ለምን እይባርከበትም? ለምንድን ነው? መስቀሉ እኮ ነው፡፡ የሠራው አንጥረኛው ነው፡፡ የሸጠውም ነጋዴው ነው፡፡ ቄሱ ብቻ በእጁ ሲይዘው ማባረኪያ የሚሆነው ለምንድን ነው? የመባረክ ሥልጣን ያለው ቄሱ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ እና ያ ቄስ ደግሞ እግዚአብሔርን ክካደ በረከት የለውም ማለት ነው፡፡ በትንቢተ ሚልክያስ "እናንተ ካህናት በረከታችሁን እረግማለሁ እኔም በረከቱን ለእናንተ ለወጥዋለሁ፡፡" ይላል፡፡

ጥያቄ ፲፫፦ውግዘት ከተላለፈ ወዲህ ብዙ እናት አባቶች፣ እኅት ወንድሞች ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ አሉ፤ እነዚህ ሰዎች፥ እንደተወገዙ ነው የሞቱት ወይስ ተፈተው፤ ይኼንንም እንዲያብራሩልን?

መልስ፤ትእዛዜን አክብረው ከሆነ ተፈትተዋል። ካላከበሩ ግን እስረኞች ናቸው።

ጥያቄ ፲፬፦ይኼን ውግዘት በግል ጋዜጣ ከማስተላለፍዎ በፊት ለምን በየቤተ ክርስቲያኑ ተገኝተው ለምእመኑ አላስተላለፉም?

መልስ፤እኔማ ታግጃለሁ። ስለታገድኩ እኮ ነው በግል ጋዜጣ ለመተንፈስ የሞከርሁት እንጂ ይህንንማ ዕድል ካገኘሁ ለምን በጋዜጣ እናገራለሁ። በመድረክ ላይ ነው የምናገረው። ጥር ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መድረክ መበደሌን ተናግሬአለሁ። ከዚያ ቀደም ብሎም አንድ ጊዜ ሙሉ ሲኖዶሱ እንዲያየው በደብዳቤም በቃልም ተናግሬያለሁ። እምቢ አሉ ነው። እንደ ጌታ ቃል ነው ያወገዝኳቸው። ከዚያ ወዲህ አልሄድኩም። መጀመሪያ ጠይቅ። እምቢ ሲሉ ለቤተ ክርስቲያን ንገር። ከዚያ በኋላ አውግዝ ነው ያለ። እንዳዘዘኝ ነው ያደረግሁት።

ጥያቄ ፲፭፦ ይኼ ውግዘት እስከመቼ ነው የሚቆየው፤ ለምን?

መልስ፤እስከሚፈታ ድረስ። ነገሩ ውሳኔ ካላገኘ ያው ነው። አርዮስ ተፈቷል? መቅዶንዮስ ተፈቷል? ንስጥሮስ ተፈቷል? እሁንም በዚህ ዓለም ብቻ አይደለም። በመጪያኛውም ዓለም ውጉዛን እሱራን ናቸው። በሥልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እሱራን ውጉዛን ይሆኑ።



ጥያቄ ፲፮፦ ብዙዕ አባታችን የግል ጋዜጣ ግዜታችሁ አታንብቡ ብለው አውግዘዋል፤ የእርሶ ውግዘት የተላለፈው ደግሞ በግል ጋዜጣ ነው፤ ይኼ ሊጋጭ አይችልም ወይ?

መልስ፤ምንያጋጨዋል? ፤እላቸውም እንዳመጹ ናቸው። እኔም ከእግዚአብሔር ጋር እንደቆምኩ ነኝ። ምን ይጋጫል? መጀመሪያ ጸባያቸው የማይሆን ሆኖ ወጡ። ከወጡ በኋላ የሚያደርጉት ነገር የላቸውም። እውነት ከሆነ ውግዘቱን ለማገድ ከመሞከር ወይም የግል ጋዜጣ አታንብቡ ብሎ ከማስገደድ፤ የሊቃውንት ጉባዔ ከማገድ፤ ሲኖዶሱን ከማፍረስ ይልቅ፤ የሊቃውንት ጉባዔውም እንዳለ ሲኖዶሱም እንዳለ እኔን አቅርበው መጠየቅ ነበረባቸው። እውነቱ ይሄ ነው።

ጥያቄ ፲፯፦ ካህናት ለምን ይወገዛሉ? አጥፊው ሌላ ነው? ደግሞም ከሥራ ቢፈናቀሉ ችግር ላይ ይወድቃሉ።

መልስ፤ከቤተ ክህነት የሚያገኙት ገንዘብ የለም። ለልብሳችን፣ ለምግባችን፣ ብለው ሊያመካኙ አይችሉም። ደግሞ ከዚህ ነጻ ካልወጡ ካህናት አይደሉም። ጌታ ራሱ፤ አንድ ባሪያ ለሁለት ጌታ መገዛት እንደማይችል እናንተም ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ልትገዙ አትችሉም ነው ያለ። ይህንን ሲያብራራ ነገሩን በዚህ ብቻ ሳይወሰን ምክንያቶቹ ገንዘብ ፍለጋ የሚሰዱን ልብስና ምግብ ስለሆኑ ምን እንበላለን? ምን እንለብሳለን? ብላችሁ አታመካኙ ወፎችን አበቦችን እዩ ብሎ በገንዘብ ምክንያት ከእሱ እንዳንለይ አዟል። ከዚህ በላይ ካልሄድን እንኳን ካህንነቱ ምእመንነቱም አይሆንም። ካህናትማ ከዚህ በላይ መሄድ አለብን። አንድ በጐቹን ለመጠበቅ የተሰየመ እረኛ አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ ከአራዊት ጋራ ተከላክሎ በጐቹን ማዳን አለበት። እሱ መሞት አለበት እንጂ እነሱን አሳልፎ መስጠት የለበትም። እንኳን ለጥቅም ብሎ አሳልፎ ሊሰጣቸው ስለህይወቱም አሳልፎ ሊሰጣቸው ነው የታዘዘው። ጌታ ራሱ"ስለ በጐቼ ራሴን እለውጣለሁ ነው ያለ። ይህንንም ለሐዋርያቱ ለካህናቱ ሊያስተላልፍ ራሱን ለወንድሙ ለውጥ አድርጐ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር ምን አለ?" ብሎ ነው እንድንቀበለው ያዘዘን። የቤተክርስቲያኒቱ ሰዎች የሆንን ሁሉ አስተማሪዎች የሆንን

ሁሉ ስለምእመናን ራሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ተጠይቀናል፡፡ እንኳን በምግብ በልብስ ልናመነኝ ይቅርና፡፡

**ጥያቄ ፲፰፦ከሁለት አንዳችሁ ከዚህ ዓለም በሞት ብትለዩ ወግዘቱ እንደታሠረ ይቀራል ወይስ ይፈታል?**

መልስ፤ እንደታሰረ ነው ማንም አይፈታውም፡፡ ቤተክርስቲያን እስካልተመለሰች ድረስ አይፈታም፡፡ ቤተክርስቲያን ተመልሳ ሲኖዶሱ የክርስቶስ ተጠሪ ካልሆነ ምንጊዜም አይፈታም፡፡ የክርስቶስ የሆኑ ጳጳሳት ከሌሉ፡፡ አሁን ያሉትም አይሆኑም፡፡ ይሄን ይወቁት፡፡ ለዚህ መድኃኒቱ ምእመናን ተሰብስበው ካህናቱንም አስገድደው፣ እሺ ያሏቸውን በውድ እምቢ ያሏቸውን በግድ ለይተው አስወጥተው አባ ጳውሎስን አውግዘው፣ ራሳቸውን አስተካክለው ካልቆሙ በስተቀር ቤተክርስቲያን አሁን የለችም፡፡ እንዲህ በመላም ደግሞ አትመለስም፡፡ አባ ጳውሎስ ድንገት ቢሞቱ፣ እኔም ድንገት ብሞት ያሉት ጳጳሳት፣ ያሉት ካህናት ተመልሰው ተክተው የሚሠሩት ምንም ዋጋ የለውም፡፡ ፍርድ ሳይፈረድ፣ አጥፊውና አልሚው ሳይለይ በምንም ዓይነት የሚደረገው ነገር ሁሉ ዋጋ የለውም፡፡ለዚህ ነው ዓመት ሙሉ የሙኘሁት፡፡ ነገሩ ጥብቅና ከባድ ስለሆነ ነው፡፡ ሰውማ ቢኖረን እኮ በሁለትና በሦስት እንኳ ይሆን ነበር፡፡ ሌላ ቀርቶ አባ ጳውሎስ ቢሞቱ ሌላ ጳጳስ ለመሾም እነዚህ በዚያ ህግ ላይ የፈረሙ ሁሉ የመሾም መብት ስለሌላቸው ያልፈረመ ጳጳስ ሦስት ከሌለ ቤተክርስቲያኒቱ ሌላ ፓትሪያርክ መሾም አትችልም፡፡ ይሄን ይወቁ፡፤ እንደገና ወደ ግብፅ መሄድ ነው፡፡የእኔ አቤቱታ ሥርዓቱ ይስተካከል ወደነበረበት ይመለስ ነው፡፡ ከተመለስ ተልቧል፡፡ ውግዘት የለም፡፡ ካልተመለሰ ግን ማንም ሊፈታው አይችልም፡፡ እንዴ! ክር አይደል፡፡ ሽቦ አይደል፡፡ ገመድ አይደል፡፡ ቃልድ ነው እንዴ?



## ከዓለም አይደላችሁም

የአባቴ ግዝትና አስቀድሞ በመንፈስ እግዚአብሔር እየተመራ የተናገራቸውየቤተ ክርስቲያን ሽኩሞች ሁሉ ሳይውሉሳያድሩ ተፈጽመዋል፡፡አስተዋይ ልቦናና ቁርጥ ሃይማኖታዊ ቅንዓት ላለው ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እየተካሄደ የነበረውን ጥፋት ለመገንዘብ እጅግም የሚከብድ አልነበረም፡፡ የፓትሪያርኩ እምባገነናዊ እርምጃ ደግሞ ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ሁሉ ገዝፎና ጐልቶ የሚታይባቸው ብዙ ጉዳዮች በይፋ መከናወናቸው የሰስት ተዕለት የቤተክህነቱ ሥራ የኖ መታየቱ እንደ መደበኛ ተግባር ተቆጥሮ ነበር፡፡

በአስራ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት ውስጥ ከተከሰቱ አሳሳቢ ጉዳዮች አንዱ በጥር ወር ፲፱፻፹፱ ዓመተ ምሕረት በአዲስ አበባ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመው የባህታዊ ፈቃደ ሥላሴበግፍ መገደል ነበር፡፡ አባቴስለባህታዊው መገደል የተሰማውን ስሜት ሲገልጽ "በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ውስጥ፣ በእውደ ምህረት ላይ ታቦተ እግዚአብሔር በቆመበት ሰው ሊገደል የቻለው፤ ከደርግ ዘመን ጀምሮእያደገ የሄደው የቤተክህነቱ ብልሽት፤ወደ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ ነው፡፡" ብሎ ነበረ፡፡ በተጨማሪም፤

"...እንደኔ አስተሳሰብ ከሆነፓትሪያርኩም ሆኑ አብረዋቸው የነበሩት ጳጳሳት፤ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት በክህነት ማገልገል አይችሉም፡፡ ይህን ሰውዬ የገደለ ማነው? ያስገደለስ ማነው? አእምሮ ካለን ገዳይ አስገዳይም አንድ ወገን አደሙ ውስጥ የገቡ ስለሆኑ በክህነት ማገልገል አይችሉም፡፡ ከክህነት ወርደዋል፡፡ ነፍስ ገዳዮች ናቸው ማለት ነው፡፡...ምእመናንንም ግማሹ እኔን ምን አገባኝ እያሉ፤ ግማሹ ቅዳሴ ካልጐደለ፣ ቃጭል ማቃጨሉ፣ ደወል መደወሉ ካልቀረ ምን አለበት እያሉ ዝም በማለታቸው፤ ሌሎች ደግሞ እሱን ምን አገባውና ነው የሚያወግዘው? ምን ጥልቅ አድርጎት ነው? እያሉ የሚያሾፉ የጥቅም ተካፋዮች ሆነው በመቀመጣቸው እነሆ በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምህረት ላይ ደም ሊፈስ ችሏል፡፡... " በማለት ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓመተ ምሕረት በወጣው ኢትኦጵ ጋዜጣ ሀሳቡን ገልጿል፡፡

ከነባሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት ያፈነገጡ፣ አንድን ሰው ብቻ በማወደስና በማሞገስ ላይ የተመሠረቱ ነገሮች መታየታቸው ከቀን ወደቀን እየጨመረ በነበረበት ወቅት፤ ከዚያ አልፎ ተርፎ ለእግዚአብሔር ክብር የተነገሩ የምስጋና ቃላትን ለሰው እስከመስጠት የተደረሰባቸው ሁኔታዎችም ታይተዋል ።

ፓትርያርኩ ከተሾሙ ጊዜ ጀምሮ ሥራዬ ብለው የያዙትን የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት የመጋፋት፣ አልፎ ተርፎም የመለወጥ ተግባር የሚቃወም አልነበረም። ለእምነታቸው ዘብ መቆም የነበረባቸው ጳጳሳት፣ የቤተ ክርስቲያን አለቆች፣ ካህናትና ዲያቆናት "ከእኔ ሌላ አምላክ አይኑርህ" የተባለውን ህግ ተላልፈው ተገኙ። ይልቁንም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታይቶ ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፓትርያርኩን ከሰውነት ደረጃ ወደ አምላክነት ደረጃ አውጥተው ለማሳየት የሚጣጣሩ ሆኑ። ይህን አስመልክቶ ይፈጽሙት የነበሩ እንቅስቃሴዎችም በተለያዩ መንገዶች ይገለጹ ነበር። በቤተ ክርስቲያኒቱ ጋዜጦች ላይ በሚወጡ ጽሑፎችና በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ በሚደረጉ ንግግሮች ላይም በይፋ የሚንጸባረቁ ነበሩ።

ሲሻው ስድብ፤ ሲሻው ደግሞ ከንቱ ውዳሴ በማዝነብ የተካነው "ዜና ቤተ ክርስቲያን" ጋዜጣ "የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ራሱን "መርሐ ተዋሕዶ" ብሎ የሚጠራውን ጸረ ቤተ ክርስቲያን ቡድን አወገዙ"በሚል ርዕስ ሥር መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባወጣው ጽሑፍ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባዔ አባላት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት አባላትና የየአጥቢያ ቤ/ክ ሠራተኞች በተገኙበት ስብሰባ ላይ የቀረበ ጽሁፍ ብሎ ይፋ ያደረገው ሰነድ የሚከተለውን ይመስላል።

"ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ሆይ፣ ከላይ በርዕሱ እንደተጠቀሰው "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው። ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ፣ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ" በማለት ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ አስቀምጦታል። ይህ አባባል ቅዱስነትዎን ያስማመንታት የሚመሰክት ነው። ምክንያቱም የጌታ መንፈስ በቅድስናዎ ላይ አድሮ እንዳባትዎ ዮሐንስ አፈወርቅ በሚጣፍጥ አንደበትዎ ሕሊና የሚመስጥ ስብከትዎ



ድሀ ሀብታም ሳይለይ የሰውን ኃጢአት ከጀርባ ላይ ሲወርድ እየተመለከቱ ክብር በተሞላበት እልልታ እየታጀበ ሲያደንቀው አይተናል።... እግዚአብሔር ሥራህን ተቀብሎታልና ሂድ እንጀራህን በደስታ ብላ የወይን ጠጅህንም ጠጣ። ሁልጊዜ ልብስህ ነጭ ይሁን ቅባትም ከራስህ ላይ አይታጣ። መክብብ ፱፥፯። ... ይህም የዘወትር መንፈሳዊ ሥራዎ ነው። ከዚህም በላይ ልብስህ ነጭ ይሁን በማለት ጥልቅ በሆነ ዕውቀትዎና በመስኮተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የሚመስል ልብስዎ በደብረ ታቦር በዛሬው ዕለት የተጀመረው ዓመት የሰላም የፍቅርና የጤና እንዲሆንልዎ እየተመኘን ምንም ጊዜም ቢሆን በስራም ሆነ በማንኛውም ኢጋጣሚ ከጐንዎ መሆናችንን እያረጋገጥን ሥነ ጽሁፋችንን በዚህ እናበቃለን።"

ይህ ከላይ የቀረበው ጽሑፍ እንደሚያሳየው ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩትን ኃይለ ቃላት ለፓትርያርኩ የተነገሩ ናቸው እስከ ማለት የተደረሰበት ነው። የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባዔ አባላትም ለአባ ጳውሎስ የአምላክነት ክብር መስጠታቸውን የሚያሳይ ሲሆን የድርጊቱ ፈጻሚዎች ምን ዓይነት የሃይማኖት ድቀት እንደደረሰባቸው ተጨባጭ ምስክር ነው።እንዲህ ያሉትን ፓትርያርክ፣ ጳጳሳት፣ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባኤ አባላትና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሰማውገዝ እንኳን አባቴ በነበረበት የክህነት፣ የዕውቀት፣ የኃላፊነትና የእድሜ ደረጃ የደረሰ ክርስቲያን ይቅርና የቤተ ክርስቲያንን ልጅነት ያገኘ ምእመን ሁሉ ይቃወምና ይለይ ዘንድ የተገባ ነበር። ለዚህም ዓላውያን ነገሥታትን እየተቃወሙ ለእግዚአብሔር ክብር ብለው የተፋለሙ፤ ከብሉይ ዘመን የዳንኤልና የሠለስቱ ደቂቅ፣ ከሐዲስም የሰማዕታት አለቃ የተባለ የኃያሉ ሰማዕት የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ እንዲሁም ቁጥራቸው የበዛ የቅዱሳን ሰማዕታት ታሪክ ይመሰክራል። ልዩነት ካለ እነሱ የተቃወሙት ነገሥታትን ሲሆን አባቴ የተቃወመው ግን ጳጳስን መሆኑ ነው።

ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ "ቤተ ክርስቲያንን የሚያውክ፣ ዓላዊ /በተናገረው የማይረጋ/ ሃሳዊ ፣ ራሱን እንደ እግዚአብሔር የሚቆጥር

በቤተ እግዚአብሔር የሚኖር እኔ እግዚአብሔር ነኝ የሚል ሰው ይመጣል" ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረውን በመጥቀስ አባቴ ተናግሮ ነበረ፡፡

"...የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት የዛሬውን ሁኔታ ስለሚመለከትና "የቅዱስ ፓትሪያርኩም አካሄድ፣ አነጋገርና በአኗኗር ያላቸው ሥርዓትና ፈሊጥ ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ ከጠቀሰው ከዚህ ሰው ፈሊጥ ያልተለየ በመሆኑ በጣም እቸገራለሁ፡፡ ..." በማለት ቅሬታውን ገልጦ ነበረ፡፡ በመቀጠልም "... ሁሉንም በራስ ፍላጐትና በዘፈቀደ መፈጸም፣ ለእግዚአብሔር ትእዛዝ አለመገዛት፣ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየተላለፉ ተሹመው ለራስ ፈቃድ መገዛትና የግል ፍላጐት ማዘናወን፣ ይህ ሁሉ ራሱን መሲህ ከሚያደርግ ሰው የሚመጣ ካልሆነ በስተቀር እኔ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ እንደሚሉት እንደ ሐዋርያት ካሉ ሰዎች የሚጠበቅ ነው አላልም፡፡ ሌሎች አስቸጋሪ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዓለም ጌጣጌጦችን የሚመስሉ ልብሶች ... አያስፈልጉም ተብሎ ታዟል፡፡

እንደውም ቅዱስ ጴጥሮስ ጌጥ የሚገባቸውን ሴቶችን ሳይቀር ሴቶች የሚያጌጡ በወርቅ በብር በብዙ ዋጋ በተገዛ አይደለምና ከዚህ ይጠንቀቁ ብሎ አውጇል፡፡ ይህን ለማስተማር መሪ የሆነ ሐዋርያ ክኤሌክትሪክ መብራትና ከፀሐይ ጋር እየተጻባለቀ ጎድንት እየፈጠረ የሰዎችን ዓይን የሚፈታተን የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሶ መውጣት በእርግጥ የሐዋርያነት ሥራ አይደለም፡፡ በብሉይ ኪዳን አሮንን እግዚአብሔር እንዲህ አስጌጦት ነበር፡፡ በአዲስ ኪዳን ግን ወርቅ ለባሽ ሳይሆን መከራ ለባሽ ሲል ሊቀ ካህናታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአደባባይ ራቁቱን ተሰቀለ፡፡ ቅዱስ እፍረትን ንቆ፣ ጨርቅ አገልድሞ፣ ማንድ ተሸክሞ ፍኖተ መስቀልን ሲወጣ አላፈረም ነበር፡፡ ተከታዮቹንም በዚህ ዓይነት ነው የጠራቸው፡፡

መከራ ይጠብቃችኋል እናንተም ከዓለም አይደላችሁም፡፡ ዓለም የሱ የሆኑትን ይወዳል፡፡ እናንተ ግን የኔ ናችሁ ከዓለም አይደላችሁም ስለዚህ መከራ ይጠብቃችኋል" ነው ያላቸው፡፡ መራቆት፣ መራብ፣



መጠማት እንጂ በወርቅ በጨርቅ ማጌጥ የቤተክርስቲያንና የመሪዎቿ ገንዘብ አይደለም፡፡ ይህም አባ ጳውሎስን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውጪ የሚያደርጋቸው እንዱ ጠባይ ነው፡፡ እነሆ እንደበግ በተኩላ መካከል ልትሞቱ እልካችኋለሁ ተብለው ከተመረጡት መካከል የሆነ ሰው የጥይት መከላከያ እየገዛ ሲቀያይር ማየትም አሳፋሪ ነገር ነው፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ ቅድም የጠቀስኩትን የቅዱስ ጳውሎስን ትንቢት ያሳስበኛል፡፡ ራሳቸውም አቡነ ገሪማና ጭፍሮቻቸው በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ መሲሃዊ ሥልጣን ብለው ያወጁትን ሳስላስል የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ትዝታ ያመጣብኛል፡፡ሁኔታው ሁሉ አላማረኝምና አባካችሁ ብዙ አታናግሩኝ፡፡..."

## ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ

"ከቁረበች አፈረሰች፣ከተመከረች ባሰች" እንደሚባለው ሆኖ የቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት መድፈር ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ ከመሄድ በቀር የሚስተካከል ወይም ባለበት የሚጸና ነገር ሊገኝ አልቻለም፡፡ አባቴም ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለምእመናን ይሰማው በነበረው ሽክምና ኃላፊነት ምክንያት በዝምታ ሲያልፋቸው የማይቻሉ በነበሩ ድርጊቶች ላይ በየጊዜው ድምጹን ማሰማቱን ቀጠለ፡፡ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሸክም ባየው ራእይና ቆይቶም ባስተላለፈው የውግዘት ቃል ምክንያት ብዙ ዓይነት ሁኔታዎችን ያስተናገደው አባቴ ጠለቅ ያለ ትምህርትና ማብራሪያ ይፈልጉ የነበሩ ምእመናን በብዛት ይጐበኙት ነበር፡፡ ትምህርት ፈላጊዎችና ጠያቂዎች በመምሰል፣ በተደራጀ ሁኔታ እየተሰባሰቡ ከመኖሪያ ቤቱ ድረስ በመሄድ ሽጉጥ እስከ መምዘዝና ሁከት እስከ መፍጠር የሞከሩ ሰዎችም አጋጥመውታል፡፡

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓት አምልኮትና የውጪ ግንኙነት" የተሰኘው መጽሐፍ ለኅትመት መብቃቱን ተከትሎ አባቴ የሰጠውን መግለጫ መነሻ በማድረግ በሃይማኖቱ ሥጋት የገባው ምእመን ተቃውሞውን ይዞ ወደ አደባባይ እስከ መውጣት ደርሷል፡፡ ሆኖም ወደፊት ታሪክ መርምሮ ሊያወጣው የሚገባው ሽፍጥ በሠሩ፣ "ከኛ በላይ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያን ለአሳር ነው" ለማለት በሚቃጣቸው የሀብረተሰቡ ክፍሎች እማካይነት መሠረተ ቢሲ ወሬዎችም ይናፈሱ ነበረ፡፡ ከነሱም በመካከል፤

"በአለቃ አያሌውና በአባ ጳውሎስ መካከል የተነሳው ውዝግብ በሃይማኖት የመለያየት ሳይሆን አስተዳደራዊ ችግር ነው"፣

"አለቃ አያሌው ፓትሪያርኩን ለማውገዝ ሥልጣን የላቸውም"፣

"አለቃ አያሌው በዓለም አቀፋዊ አስተሳሰብና ትብብር ስለማያምኑ ነው የፓትሪያርኩን የቫቲካን ጉዞ የተቃወሙት"... ወዘተ የሚሉ ይገኙባቸው ነበረ፡፡



እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ሥራዬ ብለው ያናፍሱ የነበሩ ክፍሎች የታቀደ የማዘናጋት ሥራ በመስራታቸው ገና ከጅምሩ ሊቀጭ ይችል የነበረው የአባ ጳውሎስ አምባገነናዊ አስተዳደር የሃያ ዓመታት ዕድሜ እንዲኖረው ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ግንባሩን የማያጥፈው አባቴ ገና ከጅምሩ ያየውን የቤተ ክርስቲያን ሸክም ቢችል ለማስቀረት፣ ባይችል ለማቅለል ብዙ ጥረትና ትግል ሲያደርግ ኖሯል፡፡ ለቤተክርስቲያን እምነትና ክብር በመቅናት ቀን ከሌት ያደርግ በነበረው ትግል ውስጥ አንድ ቀን ሰሚ ይገኝ ይሆናል የሚል ቀና እመለካከት የነበረው በመሆኑ በመጀመሪያ አካባቢ በቤተሰባዊ ምክክርና ንግግር መፍትሔ ለማግኘት ከፍተኛ ተስፋ ነበረው፡፡

ከቤተ ክህነት ኃላፊነቱ ከተገለለ በኋላ ለምእመናን ካስተላፋቸው መልእክቶች መካከል ከዚህ በታች የሰፈረው ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን ምእመናን የተላለፈ አደራ በሐዋርያዊ ጉዞው የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የተሰጠ አባታዊ አደራ በመሆኑ እንደሚከተለው ሰፍሯል፡፡

> *"...ዛሬ አቤቱታዬን ያቀረብኩት ለእነሱ ብቻ አይደለም ለሰማይም ለምድርም ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ "ሰማይ ሰማ፥ ምድር አድምጪ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፥ ልጆች ወለድኩ አሳደግኩኝ እነሱ ግን ካዱኝ አለ፡፡ "...እኔም ባለ ሀቅሜ እግዚአብሔር በላከኝ መልእክት መሠረት ምእመናን፣ ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሃይማኖታቸውን፣ ኢትዮጵያን አገራቸውን እንዲጠብቁ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር የደረሰኝን መልእክት አስተላልፌያለሁ ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ፡፡ ሰማይና ምድር ይመሰክሩልኛል፡፡ እንግዲህ መልእክቱ በዚህ ምክንያት ነው እስከአሁን ሲታገል የቆየሁት፡፡ አሁንም በሲኖዶሱ ውሳኔ ላይ ምንም የምተችው ትችት የለኝም ሂሴን ጨርሻለሁ፡፡ ይሄ*

እንዲህ ነው የምለው የለኝም፡፡ አሁንም ደግሜ የምናገረው ግን ምእመናንም ሊቃነ ጳጳሳትም እግዚአብሔር ለዚህች ቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሰጥ አብረው እንዲጸልዩና ሁሉም ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ ላይ እንዲቆሙ ነው ጥሪዬን በድጋሚ የማስተላልፈው፡፡ ይህንን የማይሰማ ቢኖር ግን የእግዚአብሔር ቃል ይፋረደዋል እንጂ እኔ ይህን አደርጋለሁኝ አልልም፡፡ አም ብዙ ሰዎች የሚሰጡት ትችት አለ፤ አንድ ነው፤ የብዙዎቹን ድምጽ መቀበል አለበት ተራ ካህን ነው፡፡ ጳጳሳትን፣ ሊቃነ ጳጳሳትን፣ ፓትሪያርኩን ማውገዝ አይችልም ይላሉ፡፡ የሚከለክለኝ ነገር የለም፡፡ በኬልቄዶን ጉባዔ ፮፻፴፮ ቱን ኤጲስ ቆጳሳት አውግዞ የወጣው አንድ ዲዮስቆሮስ ነው፡፡ የድምጽ ብልጫ በሃይማኖት የለም ጥራት እንጂ፡፡ በጥራቱ ሕጉን ሥርዓቱን መጠበቁ ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊ ካህን ፣ የኦርቶዶክስ የሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ እንደመሆኔ መጠን ማውገዝ እችላለሁኝ፡፡

በትንቢተ ኤርምያስ ም.፳፫ ቁ.እንደተገለጠው አባታችው ያልወለደውን የሚሰበስብ የቆቅ አሙራ ወይም ያልወለደችውን የምታቅፍ የቆቅ እናት ሆነው ከተገኙ ወፎቹ ወንዱም አባታቸው ሴቷም እናታቸው እንዳልሆኑ አውቀው ተረድተው ይለያሉ፡፡ ልክ እንደ ወፎቹ ሁሉ ምእመናንም እምቢ ካሏቸው አባት እራሳቸውን ለይተው የእነሱ የሆነ ቄስ ዲያቆንና ጸሐፊ ሌላም የቤተ ክርስቲያን አባል መርጠው ከእነሱ ጋር የቆመውንና እምቢ ብለው የሄደውን ለይተው እንዲያውቁ በገንዘባቸው በአስተዳደር ላይ ቁጥጥር እንዲያደርጉ በየአድራቸውና በየሰበካ ጉባኤያቸው ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው የሚሆነውን በጥንቃቄ እንዲከታተሉ ከዛም ቀጥሎ ቅርሳቸውን እንዲጠብቁ አደራ እላለሁኝ፡፡

ምናልባት ለቤተ ክርስቲያን አልታዘዝም የሚለው ኃይል እየጨመረ መጥቶ አንድ ሰው ወይም አንድ አለቃ" ይህን ያህል አቅርብ" በተባለ ጊዜ ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን ቅርሶች እያወጣ



መስጠቱ የማይቀር ስለሆነ ከጽላቱ ሙሴ ከመስቀሉ ጀምሮ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት የሚያሰኙ በመሆኑ ምእመናን በየአጥቢያቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን የእነሱ የሆኑትን ቀሳውስትና ዲያቆናት ለይተው እንዲያውቁ ሕጋቸውን እምነታቸውንም ቤተ ክርስቲያናቸውንም እንዲጠብቁ አደራ እላለሁኝ፡፡ የኔ መልእክት ይህ ብቻ ነው፡፡[62]

አባቴ በአውደ ምህረት ላይ እንደልቡ የማስተማር ዕድል እያጣ በሄደባቸው ከ ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ጀምሮ ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለየበት እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.መጨረሻ ድረስ በነበሩት ዓመታት በመጽሔቶችና በጋዜጦች አማካይነት ምእመናንን በማስተማር በማጽናናት በማስጠንቀቅና በማንቃት ረገድ ብዙ መልእክቶችን አስተላልፏል፡፡ ያስተላለፋቸው መልእክቶች ሁሉ አጠርና ጠቅለል ባለ መልክ ይገለጡ ቢባል ዋነኛ መልእክታቸው ኢትዮጵያውያን በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ተጠንቅቀውና አክብረው እንዲጠብቁ ማሳሰብ ነው፡፡ እንደ አባቴ እምነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ክብር መጠበቅ ማለት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ክብርና ኅልውና መጠበቅ ማለት ነው፡፡ ከሕገ ልቡና ወደ ሕገ ኦሪት ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ወንጌል እየተረማመደ በያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ሲረጋገጥ ለኖረው አምልኮተ እግዚአብሔርና በዚህ አማካይነት ለተገኘው ለማንኛውም ሥጋዊና መንፈሳዊ በረከት ሁሉ ዋነኛዋ ባለ ውለታ፣ የእምነት፣ የነጻነት፣ የአንድነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የእውቀት፣ የቅርስ፣ የታሪክና የባህል መዘክር የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነች፡፡

የአባቴ እምነት በተለያዩ የአስተሳሰብ ዘውጎች ተመንዝሮ ይታይ ቢባል ደግሞ የማይነካካው ጉዳይ የለም፡፡ ሃይማኖትን፣ ሥነመንግሥትን፣ ሥነጥበብን፣ ኪነጥበብን፣ ሥነፈለክን፣ ፊደልን፣ ቋንቋን፣ ታሪክንና

[62] መብሩክ ጋዜጣ፣ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓም፡፡

ባህልን…ወዘተ ይዳስሳል። ከነዚህ ሁሉ የአስተሳሰብ ዘውጎች ውስጥ ሃይማኖትን ብቻ እንኳብንወስድ በሃይማኖት ላይ አባቴ ያስተማረውን ሁሉ በአንድ መጽሐፍ ቅጽ ለመጨረስ የማይታሰብ ነው። "በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" ብሎ በኦሪት በፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፩ የሚጀምረውን መጽሐፍ ቅዱስ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር [illegible] አሜን።" ብሎ እስከሚጨርሰው የራእይ ዮሐንስ መጽሐፍ ድረስ ምዕራፍ በምዕራፍ እየሄደ አስተምሯል። ትምህርቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖናና ሥርዓት የጠበቀ እንዲሆን፤ እንዲሁም ለትውልድ እንዲተርፍ በማሰብ ደከሞበታል። ቀኖናና ሥርዓት ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተርፍ መድከሙ እንዲያው ለማውረስ ብቻ በሚል ፈሊጥ ሳይሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ምእመናንን ወደ ዘለዓለማዊ ክብር የምታደርስ ትውንተኛዋ ፍኖተ ሕይወት ነች ብሎ ስለሚያምንም ነበረ። ሁሉም ምእመናን በሃይማኖታቸው እንዲጠቀሙ፣ እንዳይጠፉ ለማድረግ ይሰማው ከነበረ ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት የተነሳ ሥጋዊና መንፈሳዊ ህይወታቸው የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት እንዲሆን ለማትጋት በማስተማር፣ በመምከር፣ በመገሠጽም ብዙ ደክሟል።

ፍኖተ ሕይወት፣ ለንዱ እመቤት፣ እጥፍ ድርብ እናት…እያለ በወትር የሚያሞግሳትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሙሉ ነጻነት ባለቤት ለማድረግ ብዙ ተጣጥሯል። እሱ ባለፈባቸው በሦስቱ ሥርአተ መንግሥቶች ከታዘበው በመነሳት በቤተ ክህነትና በቤተ መንግሥት መካከል ሊኖር ይገባዋል ብሎ የሚያመንበትን ምክር ደጋግሞ አስተላልፏል። ለምሳሌ ያህል"ሙዳይ" በሚል ሥም ይጠራ ለነበረ መጽሔት በሰጠው ቃለ መጠይቅ ላይ፤

"የመንግሥትና የቤተ ክህነት ግንኙነት ምን መሆን አለበት ይላሉ?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ከዚህ የሚከተለውን መልስ ሰጥቶ ነበረ።

"መንግሥትና ቤተ ክህነትማ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ተለያዩ። ሆድና ጀርባ ሆኑ። ትልቁ በሽታ የተፈጠረው ከዚያ ወዲህ ነው። የአብዮት ዘመን



አብዮተ የዛር ዘመን ነው። ቤተ ክርስቲያን ጠፋች። እግዚአብሔርና ኢትዮጵያ ተፋቱ። የተማሩ እየተጣቡ ያልተማሩ ተሾሙ። ማን በሞተበት ማን ይበላል? ተባለና ሹመቱ ሁሉ ለሌላ ሆነ። እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቀረች።

አሁንም እንደጠፋች ነው። እቧን መልሶ ለመውለድ በቅድሚያ ራሳቸውን ለመንፈሳዊ ዓለም በሃቅ ያስገዙ ካህናትና መነኰሳት ያስፈልጓታል። መንግሥትም በውስጥ ጉዳይዋ ጣልቃ መግባት የለበትም። ሲቸግራት ቢረዳት፣ አቅሟ ሲደክም ቢደግፋት ክፋት የለውም። በፖለቲካ መግርያነት ግን ሊጠቀምባት አይገባም። እሷም ብትሆን ሳይጠሯት እቤት እያለች ሕዝብ ለጠላቸውና በጉልበት ሥልጣን ላይ ለወጡ መሪዎች ማጐብደድ የለባትም። የግንኙነቱ መሥመር ይህን ነው መምሰል ያለበት።" ሙዳይ፣ ጥቅምት ፲፱፻፹፩ ዓ.ም.

ከሃይማኖት ጉዳይ ቀጥሎ በአባቴ በትምህርቶች ውስጥ እጅግ ገዝፎ የሚታየው ሌላው መልእክት "ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነትንና አንድነትን"የሚመለከት ነው። በመጻሕፍቶቹ፣ በመንፈሳዊ ብዙሐን፣ በተለያዩ ትምሕርታዊ መድረኰችና በመቅረጸ ድምጽ በተመዘገቡ መልእክቶቹ ውስጥ በዚህ ጉዳይ ላይ በርከት ያለ ትምህርት ሰጥቷል። ከላይ በተጠቀሰው መጽሔት ተመሳሳይ ዕትም ላይም "የዛሬዋን ኢትዮጵያን እንዴት ይገልጿታል?"ተብሎ ለቀረበለት ጠያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቶ ነበረ።

"ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ሁሉ ኢትዮጵያ እንዴት ተገኘች? የማን ናት? እንዴት ኖረች? ብሎ ወደ ኋላ በመመለስ ታሪክን መቃኘት ያስፈልገዋል። እንዲህ ካልሆነ የኢትዮጵያ መድኃኒት አይገኝም። ትልቁ ችግር የፖለቲካ ሰዎች በልባቸው የተቋጠረውን ነገር ብቻ በሌላ ላይ ለማሳደር ሲሉ እራሳቸውን አሞኝተው ሌላውን ለማሞኘት የሚያደርጉት ጥረት እንጂ ኢትዮጵያዊነት ብዙ የሚያከራክር አይደለም። ይህቺን የበላ ይህቺን ያገኛል ከሚለው የመንገድ ላይ ቁማር ጨዋታ ተለይቶ የሚታይ አይደለም የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ፖለቲካ፡፡ በዚህ አይነት ግርግር ውስጥ የምትገኘዋ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያም የቁማርተኞች መድረክ እንዳትሆን እሰጋለሁ፡፡ እግዚአብሔርና ሕዝቧ ካልጠበቋት በቀር አገሬ ገደል ጠርዝ ላይ የቆመች ትመስላለች፡፡"ሙዳይ፡ጥቅምት ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.



## በእሳቱም በውሃውም መካከል እናመሰግንሃለን

ወጣቱ ትውልድ ለአገሩ ታሪክ ባዕድ የመሆን ነገር ገና ከጅምሩ ምንያህል አባቴን ያሳሰበው ነበረ፡፡ ከማኅበረሰብም ባለፈ የፈራውና የሰጋበት ሁሉ ተፈጽሞ ያየ ሰው በመሆኑ የኢትዮጵያን ታሪክ በማስተማር ረገድ በምሑራን አካባቢ ቸልታ እንዳይኖር ለማስጠንቀቅ ሞክሯል፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡

"ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለው በምሑራን ላይ ነው፡፡ በአገሪቱ ላይ ለሚደርሰው አደጋም ሆነ እድገቷን አስመልክቶ ለሚመጣው ጥያቄ በግንባር ተጠያቂዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡ ከትናንት ስህተታቸው ተጸጽተው ዛሬ ለጥፋት የተዳረገችውን ኢትዮጵያን ካንገበገበባት አደጋ ለማዳን መረባረብ አለባቸው፡፡ ከሦስት ሺህ ዘመን በላይ ዕድሜ ያለውን ክቡር የኢትዮጵያ ታሪክ በየደረሱበት ማስተማርና ህዝቡን በአንድነት ጥላ ሥር ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ መጽሔቶች ጋዜጦች መጻሕፍት ራዲዮና ቴሌቪዥን ድምጻቸው ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ!ኢትዮጵያ!የሚል ቢሆን እመርጣለሁ፡፡ በያለንበት ስለ አንድነት ስለ ፍቅር ስለ ሰላም ከመስበክ ወደኋላ አንበል፡፡ ለአገራችን ስንል ነገ የምንሞተውን ሞት ዛሬ ብንሞት ጽንቅ እንጂ ኃጢአት አይደለም፡፡ ..."[63]

ነገረ መንግሥትን (ፖለቲካን)አስመልክቶም አባቴ የራሱ የሆነ እምነት ነበረው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከመገናኛ ብዙኀን ለቀረቡለት ጥያቄዎች ከሰጣቸው መልሶች ውስጥ ስለ ነገረ መንግሥትና ሃይማኖት ከተናገራቸው ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

"የቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ባየውና በሰማው ሁሉ ሰው ይሰማኛል አይሰማኝም፣ ይቀበለኛል አይቀበለኝም አይልም፡፡ የእግዚአብሔር ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መልእክት ማድረስ ግዴታው ነው፡፡ ይህ ስለሆነ እኔም ግዴታዬ ነው፡፡

[63] ሙዳይ መጽሔት፣ ጥቅምት ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.

ብዙ ሰዎች "አያሌው ሲናገር ትምህርቱን ከፖለቲካ ጋር ባይቀላቅል ጥሮ ትምህርቱ ጥሩ ነበረ" ብለው የሚተቹ አሉ፡፡

አንዳንዶችም አግባብ አይደለም ብለው ሙሉ ለሙሉ የሚቃወሙ አሉ፡፡ እኔ ግን የማምንበት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ፖለቲካና ሃይማኖትን የሚለያያቸው ነገር የለም የሚል ነው፡፡ ...ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ የእግዚአብሔር አገር እንደመሆኗ መጠን በመንግሥትም ሆነ በጠቅላላው አስተዳደር በሕዝባዊ ኑሮም ሆነ በእመራሩ ክፍል ንጹሕ ፖለቲካ የሚባል ነገር የለም፡፡ ፖለቲካ በኋላ ብልጦች የሠየሙት ሥያሜ ነው፡፡ ይህ ስለሆነ በሃይማኖት አስተማሪ ኑሮ ላይ ፖለቲካ የሚባል እንቅፋት ሊደቀን አይገባውም፡፡ ያንን ተራምዶ ካልሄደ ደግሞ ያ ሐዋርያ አይደለም፡፡ መረመድ አሰበት፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ከክርስቶስ የተሰጠው መልእክት "እሳትም ማእበልም ቢሆን አያቃጥልህም፡፡ ማእበልም ቢሆን አይቆርጥህም፡፡ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ የሚል ነው፡፡ ይህንን አይተው የቀመሱት ደግሞ "በእሳቱም በውሃውም መካከል እናመሰግንሃለን" ነው ያሉት፡፡ እኔም የምከተለው ይኸው ነው፡፡ ምናልባት በተፈጥሮ ጓደኞቼ ወንድሞቼ በጠባይ ግን ከእኔ ለየት ብለው የሚመለከቱኝ ሰዎች "እውር ነህ መንገዱን አታውቅም ቢሉኝም በዳሰሳም ቢሆን የምሄድበት መንገድ ይኼ ነው፡፡ ይህቺን እግዚአብሔር የሰጠኝን በትረ ሃይማኖት እያንኳኳሁ አውሬውም ጋኔንም ከመንገድ የሚለቀው እየሰቀቀ ፣ የማይለቀውም እየደቀቀ መንገዴን የምሄደው በዚህ አቅጣጫ ነው፡፡ በዚህ ፖለቲካ አይገድበኝም፡፡ በፖለቲካ አልታገድም፡፡ "[64]

ከአባቴ እውቀት በጥቂቱም ቢሆን ጨልፎ ለትውልድ ጥቅም በማስቀመጥ ረገድ የአሜሪካ ድምፅ ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ ተጠቃሽ የሚሆን ሥራ ሠርቷል፡፡ ከአባቴ ጋር በብዙ ጉዳዮች ላይ የመነጋገር ዕድል ባገኘበት አንድ አጋጣሚ ስለ ነገረ መንግሥትና ስለ ሃይማኖት ጠይቆት ነበረ፡፡

[64] መገር ጋዜጣ፡ ሚያዚያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.



ስለ ፖለቲካና ሃይማኖት ሲነሳ ብዙ ሰዎች "የሃይማኖት ሰው ፖለቲካ ውስጥ ምን አገባው? ፖለቲካና ሃይማኖት አብረው አይሄዱም" የሚሰነዝሩትን ነገር ለጥያቄው መንሰዔ በማድረግ አዲሱ ለአባቴ አቅርቦ ነበር፡፡ ይህን ጥያቄ መሠረት በማድረግ አባቴ መልስ ሲሰጥ፤

ነገረ መንግሥትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸውን አንድምታ ከመሠረቱ ከሕገ ኦሪት ጋር አዛምዶ ረጅም ማብራሪያ ሰጥቶታል፡፡ ቀዳማዊ ምኒልክ ታቦተ ጽዮንን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ጊዜ በአያቱ በንጉሥ ዳዊት ሥርዓትና ቃል መሠረትነት እሱ የእግዚአብሔር ባሪያ አገልጋይ ሊሆን ቃለ መሃላ ሲገባ ካህናትም በአባቶቹ ሥርዓት ሲጠበቁት ቃልኪዳን እንደገቡለት በማብራራት ይህ ሥርዓት እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ መድረሱን ገልጾለታል፡፡

በኢትዮጵያ ማንኛውም ሰው ከነገረ መንግሥት ሊገለል አይችልም የሚል አቋም የነበረው አባቴ በተለይ ካህናት የአምልኮተ እግዚአብሔር ጉዳይ ጉዳያቸው የመሆኑን ያህል የነገረ መንግሥት ጉዳይም ጉዳያቸው ሊሆን እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥቶታል፡፡ እንደ አባቴ እምነት ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታለት የኖረችው አምላክ ከሌለ፤ የኢትዮጵያ ሕይወት የለም፡፡ በዚህ ምክንያት ማንኛውም ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ደረጃ ያለ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በዚህ ጉዳይ ውስጥ በይፋ በግልጽ ገብቶ ሊናገርበት፣ ሊመሰክርበት አልፎም ሊሞትበት ይገባል በማለት ይገልጻል፡፡

አባቴ የቀደሙ አባቶቻችን በብዙ ጥረትና መስዋዕትነት ያስረከቡንን ቅርሶችና ውርሶች ጥለን ሳይሆን ይዘን ወደ ፊት መራመድ ይገባናል የሚል እምነት የነበረው፡፡ አብዝቶ ከተሟገተላቸው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ቅርሶችና ውርሶች መካከልም የግእዝ ቋንቋ ዋነኛው ነው፡፡ የግእዝ ቋንቋ የ"አፍሮ ኤዢያ "ዘርፍ የሆነው "የሴሜቲክ" ቋንቋዎች ቤተሰብ ነው የሚለውን አስተሳሰብ አባቴ አይቀበለውም፡፡እንደ አባቴ እምነት ግእዝ የቋንቋ ሁሉ መሠረት ነው፡፡እንደ እርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ግእዝም የራሱን ጠላቶች በጉያው ይዞ ኖሯል፡፡ በመሆኑም በራሱ በግእዝ ፊደል አፋቸውንና እጃቸውን አፍታተው

መልሰው መቃብሩን ለመቆፈር ከተነሱ ኢትዮጵያውያን ጋር አባቴ ብዙ ሙግት ገጥሟል፡፡

ግዕዝን የመጀመሪያው ሰው አዳምና መላእክት ከእግዚአብሔር ተምረውታል፡፡ እንደመላእክት በተፈጥሮው አዋቂ ሊሆን ጸጋ ተሰጥቶት የነበረ ሰው ከገነት ከተባረረ በኋላ ዕውቀቱ እየደከመ በመሄዱ የአዳም ሦስተኛ ትውልድ በሆነው በሄኖስ ፊደል ተቀርጾለታል፡፡ "በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጣፍ ያለ ይወረሳል፡፡"እንዲሉ ከጥፋት ውሃ በፊት ከነበሩ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ውስጥ መንፈሳዊ ትምህርትን የያዘው "መጽሐፈ ሄኖክ" እና ሥጋዊ እውቀትን የያዘው "መጽሐፈ ፍልስፍና" በግዕዝ ቋንቋና ፊደል ተጽፈው ለትውልድ ተላልፈዋል፡፡

"አዳም በገነት ሳለ የፍጥረቱ ሁሉ ቋንቋ አንድ ነበረ፡፡ እሱም ግዕዝ ነበረ፡፡" የሚለው አባቴ አባብና ሔዋን በዐባብ ለመገናኘት የቻሉ ቋንቋው አንድ በመሆኑ እንጂ 'በዐይን ጥቅሻ በክንፈር ንክሻ ቢኾን ኖሮ ሔዋን ምልክቱን እስክታጠናው አዳምም ነገሩን በደረሰበት ነበረ፡፡" ይላል፡፡ በሰናኦር ግንብ የሰው ልጆች ቋንቋ እስኪለያይ ድረስ ግዕዝ ብቸኛ ቋንቋ እንደነበረም አጽንኦት ይሰጣል፡፡ በሰናኦር ሜዳ የሰው ልጆች ግንብ ለመሥራት በተሰማሙ ጊዜ የተስማሙበትን ውል በግእዝ ቋንቋ መጻፋቸውን የሚተርኩ አባቶች እንደነበሩም "የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት" በተሰኘው መጽሐፉ ይገልጻል፡፡

ከግእዝ ቋንቋ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ሥርዓትና ታሪክ፣ መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር፣ ሥነ ጥበብ ፣ ኪነ ጥበብ፣ ሥነ ፈለክና የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር፣ ዘውድ፣ ዙፋን፣ ንግሥተ ሳባ፣ ሰብአ ሰገል፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በአላት…ወዘተ…ወዘተ ሁሉ አባቴ ያስተማረባቸው፣ የጻፈባቸው፣ የተጠየቀባቸውና መልስ የሰጠባቸውናቸው፡፡ በአገራችውና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ጥናታዊ ሥራዎችን የመሥራትሙያዊና ባለአገራዊ ኃላፊነት ያለባቸው ሁሉ ቢያስተውሉ እጅግ ብዙት ያለው የእውቀት ማዕድን ሊያገኙባቸው እንደሚችሉ እምነቴ ጽኑ ነው፡፡



# ምዕራፍ ፯

## ስንብት
## ፲፱፻፺፱